# ✞ የወሲብ ፊልሞችና ጠንቆቻቸው ✞

በስመ አብ፣ ወወልድ፣ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን።

## ✞ ዝም ያለው የሚሊዮኖች ጩኸት ✞

ልቅ የሆኑ የወሲብ ፊልሞች መቼ እንደተጀመሩ በውል ባይታወቅም፤ ወደ አገራችን ኢትዮጵያ ዛሬ ላይ ተስፋፍተው፤ የወጣቱና የጎልማሳው የትውልድ ክፍል ዘመን ፈተና ሆነው ሁሉም በየግል በየግል ከራሱ ጋር እንዲጣላና የሃይማኖት አካሄዶችን እንዲሸሽ ሰፊ ድርሻ የተጫወተ የአጥፊው ጥልቁ መልአክ አባዱን ሴራ ነው።

+++

በዘመናችን በወሲብ ፊልም ያልተጠመደ ወጣትና ጎልማሳ ማግኘት አዳጋች ይሆናል። በተለይ የእጅ ስልክ በየግል በየግል አብዛኞቻችን እንደ መታወቂያ ካርድ ይዘነው የምንዞረው መለያችን ከመሆኑም ጋር ተያይዞ በቀላሉ የተለያዩ ድረገጾችን የማግኘት አጋጣሚዎች(Internet accessibility) በመኖሩ ሰዎች ሳይቸገሩ ወደ ወሲብ ፊልም ቁራኛነት በመግባት ለመውጣት ግን ተቸግረው ይስተዋላሉ።

+++

የወሲብ ፊልም ሱሰኝነት በአገራችንና በዓለም አቀፍ ደረጃ ስነልቦናዊ፣ አካላዊና ማኅበራዊ ሰፊ ቀውሶችን በወጣቱ ትውልድ ላይ ለማድረስ ሆን ተብሎ በአጥፊ መናፍስቶችና የክፋት መሣሪያ በሆኑ ሰዎች የተቀናበረ የወጥመድ መረብ ሲሆን፤ ግቡንም አሳክቶ ልክ እንደ ወረርሺኝ በብዙ አገራት በመዝለቅ ሁለንተናዊ እና ዘርፈ ብዙ ቀውሶችን ከዘመን ዘመን በሚጋሸበው ትውልድ ላይ በጥልቅ መሠረት ለማስከተል ችሏል። ስለዚህም ነገር የዮሐንስ ራእይ ምን ይላል የሚለውን እንመልከት።
(የዮሐንስ ራእይ ምዕ. 17)
---
3፤ በመንፈስም ወደ በረሀ ወሰደኝ፤ የስድብም ስሞች በሞሉበት፥ ሰባት ራሶችና አሥር ቀንዶችም ባሉበት በቀይ አውሬ ላይ አንዲት ሴት ተቀምጣ አየሁ።
4፤ ሴቲቱም በቀይና በሐምራዊ ልብስ ተጐናጽፋ በወርቅና በከበሩ ድንጋዮች በዕንቍዎችም ተሸልማ ነበር፤ በእጅዋም የሚያስጸይፍ ነገር የዝሙትዋም ርኵሰት የሞላባትን የወርቅ ጽዋ ያዘች፤
5፤ በግምባርዋም ምስጢር የሆነ ስም። ታላቂቱ ባቢሎን፥ የጋለሞታዎችና የምድር ርኵሰት እናት ተብሎ ተጻፈ።

በሴት ጾታ የተገለጸው ይህ የጥልቁ መንፈስ፤ ትውልዱን በተብለጨለጨ የዘመን ውበትና መሣሪያ አነሁልሎ፤ ዜጎች ከእግዚአብሔር አምላክ ጋር የሚኖራቸውን የቅዱስና ሕይወት በመቀንጠስ፤ በታላቅ የዝሙት ማዕበል እንዲንሳፈፉ ያደረገ የጥልቁ አለቃ የአባዶን መንፈስ ምሪት ነው።

ዛሬ ሲሆን የምናየው ሁሉ ምንድነው? ለምን ትውልዱ በወሲብ ግለት ነደደ? ለምን በመዝናኛው ኢንዱስትሪ በኩል የሚቀርቡት  ጽሑፎች፣ ዘፈኖች እና ፊልሞች ላይ የወሲብ ድርጊቶችና የራቁትነት ገጽታዎች እጅግ በዙ? ዕድሜና የአገራትን ባሕል ሳይመርጡ ለሕዝብ ያለ ማቋረጥ የሚተላለፉ የሚዲያ ውጤቶች በብዛት የዝሙት ምኞትን የሚጠሩ ስለምን ሆኑ? ለምን የአስገድዶ መድፈር ዜናዎች፣ የጽንስ ማስወረድ ድርጊቶች፣ የእርግዝና መቆጣጠሪያና ማዘግያ ዘዴዎች ከመጠን በላይ እየጨመሩ ሄዱ?

ምክንያቱም አበለጭልጫ በሐምራዊ ልብስ ተጋገጣ የተገለጸቺው የዝሙት መንፈስ፤ የመጨረሻው ዘመነ ገዜዋ ሆኖላታልና የሠራዊቶቿን የርኩሰት ጽዋ በዓለም ላይ ስላፈሰሰቺው ነው።

+++

የወሲብ ፊልሞች ሱስ ልክ እንደ ትምባሆ፣ አልኮልና አደንዛዥ ዕፆች ሱስ ከያዘ በቀላሉ የማይለቅ፤ ቀስ በቀስ በመቆራኘትም መላ የኑሮ አቅጣጫንና የውስጥ ሕይወትን መንገድ ወደ አንድ መስመር በመሳብ፤ የኢንተርኔትና ራስን በራስ የማርካት(ግለ-ሩካቤ) ተጠማጅ የሚያድርግ ያልተነገረለት እጅግ አደገኛ የመናፍስት ማፍዘዣ ነው። የወሲብ ፊልሞችን የመመልከት ልምምዱ ቀስ በቀስ እያደገና እንደ ግል ጠባይ

እየጎለበተ የዘወትር እህል ውኃ የሚሆን መላ የስሜት ሕዋስን በዝግታ እየተቆጣጠረ የሚመጣ የአእምሮ ማስከሪያ ነው። ዝሙታዊ ፊልሞችን ለመመልከት ቀላል፤ ከማየት ለመራቅ ግን ፈታኝ የሆነበት አንደኛው መሠረታዊ ምክንያት የመናፍስት ሰንሰለትና ሰይጣናዊ እገዛ ያለበት ከመሆኑ ጋር በተያያዘ፤ ግለሰቦች ከሱሱ ለመላቀቅ ብለው! ብለው! ሲሰለቻቸው፤ 'በራሱ ጊዜ ይተወኛል' እያሉ ተስፋ በማሳጣት እንዲኖሩ እያደረገ ነገን አጨልሞ ዛሬን በቁራኝነት የሚዋረስ አደንዛዥ ወረርሺኝም ነው።

+++

<< ቁራኛነት >> ከርኩሳን መናፍስት ጋር በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የሚያያዝ የጥፋት አሠራር አለው። ይህንን ጥቂት የማይባሉ ሰዎች ስለማይገነዘቡ፤ በሥጋዊ መፍትሔዎች ብቻ ተጉዘው ከጥገኝነት ችግር ለመላቀቅ በተደጋጋሚ ሲጥሩ ለጥቂት ቀናት አሊያ ሳምንታት ተሳክቶላቸው መፍትሔ ቢያገኙም፤ ዞሮ ዞሮ ወደ ተዘፈቁበት ማጥ እየወደቁ ተስፋ በመቁረጥም እንደ ልማድና አንድ የኑሮ አካል አስተናግደውት ዝም ብለው ተቀምጠዋል። ዘመናዊ ነው በሚባል በዚህኛው ትውልድም፤ ግለ-ወሲብ እንደ አንድ የሥልጣኔ ክፍል ተቆጥሮ በየትምህርት ቤቱና መሥሪያ ቤቱ ቀልድና ስላቅ እየተበጀለት፤ በውስጥ ግን እየተለቀሰለት ያለ የብዙዎች ድምፅ አልባ ዋይታ እንዲሆን የአንበሳውን ድርሻ የተጫወተው የወሲብ ፊልም ቁራኝነት ሲሆን ወጣቶች በጋራ ሲጨዋወቱ የሚስቁበት፤ በየግል በየግል ግን የሚያለቅሱበትና ራሳቸውን የሚጠሉበት አዚማዊ ጠባይ ያለው የውስጥ ድንዛዜንና ግዴየለሽነትን የሚያሰራጭ የርኩሳን መናፍስት የግብር ጭዳ የሚያደርግ የጓዳ የሚመስል የዓለም በሽታ ነው።

+++

ህቡዕ ሰይጣናዊ ድርጅቶች እንደ ኢሉሚናቲ፣ ዘ ናይት ቴምፕላርስ እና ፍሬመሰንስ ያሉት አጥፊዎች፣ ቀድመው ከጠለፉት የሴራ ድርጊቶችና የትውልድ ማደንዣዎች መካከል በሰፊ ጥናትና ዘመናትን በፈጀ የሴራ ቅንብር የተተገበረው የወሲብ ፊልም የጠምዛዥነት እቅድ(project)፤ ከፍተኛና ዓለም አቀፋዊ በጀት ተበጅቶለት፤ ዛሬ ላይ ሰለጠኑ በሚባሉ አገራት ላይ ራሱን የቻለ የመዝናኛ ማዕከል(Film industry) ሆኖ፤ ገና ከማለዳው ወጣቱን እያሰረና እያጨነገፈ፤ ከታለመለት እቅደ-ንድፍም አሻግሮ በመዝለቅ ኃልማሳና በዕድሜ የገፉ ባለትዳር የልጆች ወላጅ የሆኑ ሰዎችን ጭምር ሱሰኛ አድርጎ ያስቀመጠ ሲሆን፤ መፍትሔው ተሸፋፍኖ ያስከተለው ኪሣራ ግን የተገለጠ ደንበኛ የዲያቢሎስ ቀኝ እጅ ለመሆን ችሏል።

ከኢንተርኔት ድረገጾችም ውስጥ ከ50% በላይ ሽፋን ያላቸው እነዚህ የፍትወት ፊልሞች፣ ምስሎችና ድምፆች፤ ከየትኛውም በኢንተርኔት በኩል ከሚኖሩ ድረገጾች የበለጠ ተከታታይ ቋሚ ተጠቃሚ ሰዎች እያፈሩ መሆኑን ስንመለከት፤ የአጥፊው አባዶን ሠራዊት ትውልድን የማደንዘዙ ተልዕኮ ምን ያህል ዘመናትንና ትውልዶቻቸውን አንድ'ጋ ሰብስቦ የማሰር አሠራሩን በተሳካ መልኩ ማከናወን እንደቻለ እንገነዘባለን።

እንደ አሜርካ ባሉ አገራት እንደ አንድ የመዝናኛው ዘርፍ አውድና ይዘት ተቆጥሮ የልቅ ወሲብ ተዋናዮችን በመመልመልና በዓለምም ፊት በመሸለም የሥራ ዘርፍ አስመስሎ እንደ ማኅብረሰባዊ ልማዶች ለማስቆጠር በተደረገው የተጋድሎ ጥረት በኩልም የተለመደና የዘመን ለውጥ አንዱ ክፍል እንደሆነ በዘዴ ለማሳሰብና በሰው ልጆች ልቦና ላይ እንዲታተም ለማስገደድ በሙዚቃውና በፊልሙ ኢንደስትሪ አማካኝነት መጠነ ሰፊ ፕሮፖ-ጋንዳ ተሠርቶለትና ሕሊናን የመቆጣጠሪያ ቴክኒክ ተቀርጾለት በየቀኑ የሚሰራጭ በመሆኑ ከላይ ከባለሥልጣናት አንስቶ እስከ ታች ያሉ የሕብረተረሰብ ክፍላትን ጨምድዶ የያዘ አይነተኛ ልክፍት እንዲሆን በቀላሉ በእጅ ስልክና በላፕቶፕ ኮምፒውተሮች የመገኘት አቅሙን በማስፋት የአየር ሞገድ ምኅዋሩን በመቆጣጠር የሄዱበት ሚስጢራዊና መናፍስታዊ አካሄድ እጅግ የበዙ የሰው ልጆችን በአጭርና በተመሳሳይ መልኩ በማጨንገፍ ተሳክቶላቸዋል።

ርኩስ መንፈሶች የሰውን ልጅ ትውልድ ሕይወት ወደ ረከሰውና በኃጢአት ወደተጨማለቀው ለመለወጥ በተለያዩ መንገዶች በሥጋዊ ድክመቱ በመዝለቅ መንፈሳዊ ሕልውናውን ለዘመናት ተፈታትነውታል። ለአዳምና ለሔዋን የተሰጣቸው የበረከትና የጸጋ ማኅተም ውስጥ የተሰጠንን ታላቅ ረድኤት-ቡራኬ ስጦታን ቀልብሰው ሥጋን በማርከስ እግዚአብሔር የተቀደሰበትና ስሙ የተጠራበት ሰማያዊ አኗኗር ከሰውነት እና ቤታችን አርቀው ዘባተሎ ኑሮን እንድንኖር የጽልመት መልእክት ይፋለሙናል። በመሆኑም አመንዝራነትና ሴሰኝነት ብዙዎቻችን ከማይታዩ ተጽዕኖዋቸው ግን ከሚታይ ርኩሳን መናፍስት የኃጢአት ግብር አስፈጻሚነት ጋር የሚገናኝ ሳይሆን ሰዎች በሞራላዊ የሥነ-ምግባር መዛነፍና መበላሸት ወይም በዘመኑ አመጣጥ የሚላከክ የአጉል ዘመናዊነት ጊዜ የመዝቀጥ ውጤት ብቻ አድርገነው ፈዘን ተቀምጠናል።

+++

በተሰወሩ የመናፍስት ወጥመድ ሥር የመግባት አንደኛው ገጽታ፤ በወሲብ ፊልሞችና ምስሎች የመለከፍ እድል ውስጥ ለመገኘት፤ በአንዳንዶች ላይ ልክ እንደተፈጥሮ አጋጣሚ የተለመደ ሁነት አስመስሎ በሕሊና ውስጥ አሊያ በሌሎች ሰዎች ግፊት እያሳመነ እንዲመለከቱት በማለማመድ እንደ ሱስ እንዲቆራኛቸው የአእምሮ ወሳኝነትን ይቆጣጠራል። አንዴ እንዲመለከቱት አጋጣሚና ሁኔታው ከተመቻቸ፤ መናፍስቱ ከውስጥም ከውጪም ሆነው በመዋረስ፤ የሰው ልጆች ከተፈጥሮና ከእምነትም ምግባር የወጣ የጋጠወጥነትና የእንስሳት ጠባይ የሚንጸባረቅበት አረማዊ ምግባር እንደሆነ በልቦና ቢረዱም፤ በፍትወት እያቃጠለ በስሜት እንዲነዱ ሕሊናን እየተጫነ እንዲለከፉበት ያስገድዳል። በዚህ ጉዞ ውስጥም ሦስት ደረጃዎችን ያሳልፋሉ፦

❶ በምናብ ውስጥ የሚያውቁትን ወይም የማያውቁትን ሰው ምስል እየሳለ የወሲብ ስሜትን ይቀሰቅስባቸዋል። ወይም ከዚህ በፊት ያዩትን የወሲብ ፊልም ደግሞ ከውስጥ ያሳያቸዋል።
❷ ከሕሊና ውስጥ ሆኖ እንደግል አሳብ እያስመሰለ ልብ ላይ የሱሰኝነቱን አዚማዊ ኃይል ስለሚጽፈው፤ ውስጣዊ ውጊያውን በተፈጥሮ ስሜት ወስዋሽነት በኩል ገፋፍቶ ገፋፍቶ በመጨረሻም እንዲመለከቱ ያደርጋቸዋል።
❸ ተመልክተው ራሳቸውን በማርካትም ሲጨርሱ ወደ ልቦናቸው በመመለስ 'ምን ነካኝ' እያሉ በራሳቸው እንዲበሳጩና እንዲሸማቀቁ እያደረገ ከውስጥ ኃጢአተኛ እንደሆኑ እየደሰኮረ ከእግዚአብሔር እንዲርቁ መንገዶችን ያመቻቻል።

+++

## ✞ መናፍስት እንዴት በወሲብ ፊልም በኩል ይዋረሳሉ? ✞

### 1) ቡዳ በመሆን

ከላይ ለመግለጽ እንደምከርኩት የወሲብ ፊልሞች የጀርባ አጥንት የሆኑት መናፍስታዊ ድርጅቶች የጥፋት መናፍስቱን ለራሳቸው የተንኮል ሥራና የአመፃ ስልት ስለሚጠቀሙባቸው፤ ከኖህ ዘመን አንስቶ የነበሩት ልቡሳነ ሥጋ መናፍስት-የኔፍሊም ሠራዊት ዳግም ከጥፋት ውኃ በኋላ በድጋሚ ወደ ሰው ልጆች ትውልድ ዘልቀው የሚገቡበትን ዕድል ስላገኙ እነዚህንና የዝሙት መናፍስት እንደ ሩሃንያ አባድ የሚባሉ የጽልመት መልአክትን በግብርና በተለያየ ጭዳ በመሳብ፤ በጥንቃቄ እንደ መደበኛ ፊልም ድርሰት አዘጋጅተው በሚለቁት የወሲብ ፊልምና ምስሎች ውስጥ መናፍስቱን አዚማዊ ቡዳ እንዲሆኑ ያደርጓቸዋል። በዓይን በመመልከት ብቻ በቀጥታ ውስጣዊ ሕይወትን እንዲቆጣጠሩም ተደርገው ስለሚላኩ፤ መናፍስቱ ቡዳ በመሆን የወሲብ ፊልሙን የሚያየውን ሰው ከውጪ ወደ ውስጡ ይመለከቱታል። እነዚህ ርኩሳን መናፍስት የሰው ልጆችን ሕይወት ለመያዝና በዝግታ ለመቆጣጠር የሚፈልጉት አንድ ፊልም አሊያም ምስል ብቻ ሊሆን ይችላል። በዚህም ምክንያት ዛሬ ላይ ብዙ ሰዎች በመጀመሪያ የወሲብ ምስሎችን ያዩበት ቀንን እስከተገኙበት ዕለተ ቀናቸው እየረገሙና እየተበሳጩ መፍትሔ ባጣ አኗኗር እየዋተቱ ታስረው ታስረው ተቀምጠዋል።

### 2) ቀድሞ ውስጥ ባለ መንፈስ አዚም በመሆን

ከውስጥ ያደፈጠ ማንኛውም አይነት ርኩስ ኃይል ሲገኝ፤ ከውጪ በምናስገባው መረጃ መሠረት ላይ እየተመረኮዘ፤ የማጥፋትና ወደ መሰነካኪያው ጎዳና የሚመራ ዘዴንና ስልትን በጥንቃቄ እየቀየሰ፤ ግዜያቸው፣ ኑሮአቸው፣ ሕሊናቸው፣ እፎይታቸው የሚያለቅስ ሰዎችን እየጨመረ፤ ወደ ተስፋ ማጣትና የብስጭት አኗኗር ከማማረር ሕይወት ጋር እያንደረደረ ለስቃይና ለመከራ የተፈጠርን እስክንመስል ድረስ ይፈትነናል።።

አንደኛው ከውጪ ወደ ውስጥ የምናስገባው መረጃ ታዲያ፣ ፊልም፣ ሙዚቃ፣ ጽሑፍ፣ ንግግርና የመሳሰሉትን ነው። እነዚህ መረጃዎች ለኃጢአት ግብር መነስኤ መሆን የሚችሉ ከሆነ ያደፈጠው ጠላት ይጠቀምባቸዋል። ግለ ሩካቤ ሥጋንም እንድንወድቅበት የሚያደርጉት መንሸራተቻዎች እነዚሁ የወሲብ ፊልሞች፣ ሙዚቃዎች፣ ጽሑፎችና መሰል መረጃዎች ናቸው።
ከሠለጡኑ አገራት በከፍተኛ ግፊትና ፍጥነት እየተንሰራፉ የመጣው የወሲብ ፊልሞችና መልእክቶች ዛሬ በአብዛኛው ወጣቶች ሥልክ ውስጥ ተሰግስገው፤ እንደ አንድ የእውቀትና የመዝናኛ ክፍል በመታየት የስሜት ማብረጃ እየሆኑ ውስጣዊ ማንነታችንን እየበሉት፤ በውጪ ግን እየሳቅንና እየተጫወትን የምናስመስል ፍጥረቶች ሲያደርጉን ማስተዋል ተሳነን። የሚገርመው፣ ባለትዳሮች፣ አዛውንታንና በዕድሜ ያልደረሱ ትንንሽ ልጆችንም የሚለክፈው የወሲብ ፊልም ቁራኝነት፤ እነርሱም የእነዚህ የፈረንጅ አተላ የወሲብ ግብአቶችን እንደ ሕይወታቸው አንድ የተለመደ ክፍል ይዘውት በድብቅ ይጠቀሙበታል።

አሁን እነዚህን ፊልሞችና መሰል መረጃዎች የምታይ ከሆነ፤ ከውስጥም ያለው ጠላት በምታየው ነገር ልክ የምትጠፋበትንና ቁራኛ የምትሆንበትን ችግር ይቀርጽለሃል። ኦሪት ዘዳግም 28፥ 34 ላይ " ዓይኖችህም ከሚያዩት የተነሣ ዕብድ ትሆናለህ።" ይላል። ምን ከምትለው የተነሣ? ዓይኖችህ ከሚያዩት የተነሣ። በእውነትም ታዲያ ከምታየው የወሲብ ፊልሞችና ምስሎች የተነሣ፤ ከራስህ ጋር እየተጣላህ በግለኝነት ጸብ የምትማስን የውስጥ ዕብድ ሆነህ ትገኛለህ።

## 3) የሚዘዋወሩ መናፍስት አጋጣሚውን ይጠቀማሉ

መጽሐፍ ቅዱስ በጴጥሮስ መልእክት በኩል << ዲያቢሎስ የሚውጠውን ፈልጎ እንደሚያገሣ አንበሳ በዙሪያችሁ ይዞራል >> በማለት ከባቢያችን ላይ የሚያንዣብቡ ጠላቶች እንዳሉ ቁልጭ ባለ ቃል አስቀምጦልናል። ከሩቅ ያያችኋል አይደለም የሚለው። በዙሪያችሁ ይዞራል ነው የሚለው። እነዚህ የሚያንዣብቡ መናፍስት የወሲብ ፊልሞችንና ምስሎችን በምንመለከትበት ጊዜ ወደኛ ለመምጣት በር ያገኛሉ። ምን ማለት ነው ለምሳሌ አበባ ንብን እንደሚጠራ ሁሉ ዝንብ ቆሻሻ ይስባታል፤ እንዲሁ የኃጢአት ልምምዶችና የአመፃ ድርጊቶች በአየር የሚዘዋወሩትን መናፍስት እይታ ስለሚስብ፤ ክፉውንና የረከሰውን ምግባር በምናደርግበት ቅጽበት ውስጥ መናፍስቱ ወደ ሕይወታችን ሊገቡ የሚችሉበትን ዕድል ያገኛሉ። ወደ ባሕሪያችን ሲቀላቀሉም መጀመሪያ ሲገቡ የተጠቀሙበትን የርኩሰት ምግባር ግብር አድርገው ስለሚቆጥሩት፤ በርኩሰት ልምምድ ውስጥ እንድንቀር ግብራቸውን ከውስጥ ሆነው በግፊትና በከፍተኛ ጫና በየጊዜው በተደጋጋሚ በመጠየቅ ከእስራታቸው እንዳንወጣ በተጽዕኖ ኃይል እጅጉን ይታገላሉ።

+++

በጥልቀትና ከእግዚአብሔር አምላክ የእውነት ቃል ጋር በማያያዝ በቀጣይ በሚኖሩኝ ተከታታይ ስድስት ክፍሎች የምዳስሰውን የሚከተሉት ርዕሶች ይዤ እመለሳለሁ።
❶· የወሲብ ፊልምና የስነልቦና ጉዳቱ
❷· የወሲብ ፊልም የቱን ያህል በዘመኑ ፋሽን ዘልቆ ሄደ?
❸· የወሲብ ፊልምና የመዝናኛው ኢንዱስትሪ ተያያዥነት
❹· የወሲብ ፊልምና ከእምነት መሸሽ
❺· የወሲብ ፊልም ለአስገድዶ መድፈር ያለው ተጽዕኖ
❻· ከወሲብ ፊልም ጥገኝነት እንዴት እንላቀቅ?

## ✞ የወሲብ ፊልምና የስነልቦና ጉዳት ✞

የሃያ አንደኛው ክፍለ ዘመን የትውልድ ፈተና ሆኖ ከገዳይ በሽታዎችና ከትራፊክ አደጋዎች ባልተናነሰ የወጣቱን ማኅብረሰብ ውስጠኛ ሕይወት ክፉኛ እያጠቃና እያኮለሸ የሚገኘው የወሲብ ፊልም ሱስ ነው።

+++

በመናፍስቶችና የመናፍስት አጀንዳ ባለቸው ሰዎች የሚመራው የወሲብ ፊልም ኢንዱስትሪ ከሚፈልጉት መጠንና ፍጥነት በተሻገረ መልኩ ብዙ የዓለምን ትውልዶችን የስነልቦና ጤናማነትና መንፈሳዊ ኑሮ በእጅጉ ጎድተዋል። አልፎም ተርፎም ወጣቶች ከራሳቸው ባሕሪይና አመል ጋር መስማማት በማጣታቸው ምክንያት ለተለያዩ የአእምሮ መታወኮችና የግል ጭንቀቶች የታደረጉ ሲሆኑ፤ ለብዙ ራስን በራስ የማጥፋት መንስኤዎችም ግብአት የሆነ የርኩሳን መናፍስት የግብር እስረኛ የሚያደርገው የወሲብ ፊልም ያልተጠና ነገር ግን ከፍተኛ ውድመት ለማስከተል የቻለ ተጽዕኖ በአገራት ላይ አስከትሏል። ብዙ ወጣቶች ከቤተሰብና ቤተሰብ አዝማድ ጧሪነት ተነጥለው የወሲብ ፊልም ሱስ ጧሪ በመሆን፤ ከሌሎች እንደነርሱ እስረኛ ከሆኑ ወጣቶች ጋር ብቻ በሚያገኟት ክፍተት በፌዝና እንደ ችግር ባልተቆጠረ መልኩ የውስጥ ስቃያቸውን ሲተነፍሱ፤ በተናጠል በተናጠል ግን ከራሳቸው ጋር የሚጣሉበትን መንገድ መንፈሱ እየቀረጸላቸው አልለቅ ያለ ጥገኛ ሆኖባቸው በዝምታ እየተቸገሩ የቆዩ በመሆኑ ስቃዩን ለምደውት ዛሬ እንደ አንድ የጠባያቸው ገጽታ አስተናግደውት ይገኛሉ።

+++

የወሲብ ፊልም ጥገኝነት ለመናፍስታዊ ማነቆ ቁራኛ የሚያደርግ ሲሆን፤ ወጣቶችና ጎልማሶች ለፍትወት የተፈጥሮ ስሜት መልስ መስጠት የሚችል አድርገው በመቁጠር እንዲገቡበት ከሆነ በኋላ፤ ከቁጥጥር አልፎ በሳምንት ውስጥ ለተደጋጋሚ ቀናት ከዛ በየቀኑ በመቀጠልም በቀን ሦስት አራቴ እንዲመለከቱና ራሳቸውን በራሳቸው በማስደሰት ግለ-ሩካቤ በመጥመድ ጠፍንጎ በሚያስራቸው ጊዜ ከጥገኘነቱ ልላቀቅህ ቢሉት 'እምቢ!' የሚል፤ እየመላለሰም በፍትወት ንዳደ ስሜት በኩል እያቃጠለ ከተነሱበት ነጥብ እንዲጀምሩ በማድረግ ውስጣዊ ሰላምን የሚያናጋ፣ እረፍትን የሚበጠብጥ፣ ትዳርን የሚያኮስስ፣ የተፈጥሮ ስሜትን የሚያደበዝዝና ከራስ ልማድ ጋር ሙግት በመግጠም ሂደት ውስጥ የአእምሮ ብሎም የአካል መድከምን የሚያመጣ እጅግ ክፉ የመናፍስት እስራትን የሚገልጥ የክፉዎች መሣሪያ ነው።

## ✞ የወሲብ ፊልም ሱስኝነት የሚፈጥራቸው መናፍስታዊ የስነልቦና ጉዳቶች ✞

### 1) ጭንቀት

ዓለም በቴክኖሎጂውና በሳይንሳዊ ልቀት ጥልቅ የሆነ ለውጥ ማምጣት ከቻለችበት አንደኛው ዘርፍ መካከል የመገናኛ አውታሮች የሆኑት የእጅ ስልኮቻችን ይጠቀሳሉ። ዛሬ በእጅ ስልኮቻችን አማካኝነት በቀላሉ የምንፈልገውን ሃይማኖታዊ፣ ማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊና የመዝናኛ መረጃዎችን ማግኘት ከመቻላችን በላይ፤ እንደ ቀድሞ ዘመን መልእክት ይዞ መንከርፈፍ ቀርቶ በፍጥነትና በጥራት ርቀት ላይ ለሚገኝ ሰው መልእክትን ማቀበል የሚቻልበት መልካም አጋጣሚ ተፈጥሯል። ጥሩ ነው እግዚአብሔር ይመስገን። ነገር ግን በአጽንዖት ልናስተውልና ልንገነዘበው የሚገባው ጉዳይ በእጅ ስልኮቻችን አማካኝነት መናፍስታዊ መረጃዎች በቀላሉ ወደ ሕይወታችን ለመግባት የሚችሉበት ዕድል በዛው የመገናኛ አውታሩ ብዛትና ስፋት መጠን ልክ እንደሚፈጠር መረዳት ይገባናል። ከነዚህም በቴክኖሎጂ ጀርባ ከሚደበቁ መናፍስታዊ የመረጃና የመዝናኛ ደባዎች መካከል ዓለምአቀፋዊ ሴራ ያለበት የወሲብ ፊልም ኢንደስትሪ በወጣቶችና በጎልማሶች የአኗኗር ሁነት ጥልቅ አደጋን በመፍጠር ብዙ ተመሳሳይ ይዘት ያለውን ችግር ካስከተለበት መንገድ አንደኛው ጭንቀት ነው።

+++

ብዙ ወጣቶች የዘመኑን ፋሽንና አለባበስ ተከትለው በአንድ ላይ ታጅበው እየተሳሳቁና እየተፎገሩ ሲታዩ ደስተኞች ቢመስሉም፤ ቤታቸው ከገቡ በኋላ ግን በከፍተኛ ጭንቀት የሚባተቱ፣ የሚናገሩትና ይሄ ነው ብለው የማይለዩት ሽብር ሕሊናቸውን የሚንጣቸው፣ በእምነትና መንፈሳዊ እንድምታ በኩል ራሳቸውን ለማስቀመጥ የሚቸገሩና በዚህም ምክንያት የነፍስ መጨነቅ ውስጥ የሚገቡ ትውልዶች ቤቱ አይቆጥራቸውም።

+++

ይሄ የውስጣዊ ሕይወት ጭንቀት እንዲከተል ካደረገው መነሻ ምክንያቶች መካከል ብዙ ቤተሰባዊና አከባቢያዊ ችግሮችን መዘርዘር ቢቻልም አንደኛው የመከራ መዋጮን በማዋጣት ለተባባሰ መረበሽና ብቸኝነት የመዳረግ ሚናን የሚጫወተው የወሲብ ፊልሞችን እና ምስሎችን አዘወትሮ የመመልከት አባዜ ነው። ወጣቶቹ ገና ሲጀምሩት የሚያስደስትና ለአእምሮ የሚያዝናና ሆነው ቢያገኙትም፤ ከጊዜያት ቆይታ በኋላ መናፍስታዊ ግብሩ በሚጠነክርበትና ሱስ የመሆን እስራቱ በሚጠብቅበት ጊዜ፤ ደጋግሞ የመመልከት ፍላጎቱ በግፊት ስለሚያይል፤ ከዚህ ስሜት ለመውጣት በየቀኑ በሚኖረው ትግል ውስጥ ዘወትር ጥቂት ጥቂት እያለ የሚጨምር የጭንቀትና የመድከም ኃይል ከውስጥ ይኖራል።

+++

በአእምሮና በልቦናም ውስጥ እየጨመረና እየገዘፈ የሚመጣው ጭንቀት እየተባባሰ ከሚሄድባቸው ምክንያቶች ዋነኛው ምንድነው፤ የወሲብ ፊልም የብልጭታ ያህል መነሻን አሳብ ብቻ መንፈሱ የሚፈልግ በመሆኑ፤ በየቀኑ ወጣቶች ከሚያዩት፣ ከሚሰሙትና ከሚያነቡት ላይ በመንተራስ የሩካቤ ጫናን በመቀስቀስ ልቦናቸውን በቀጭን መስመር ላይ በማጥበብ እንዲመለከቱ በዙሪያቸው ከወሲብ ነክ እይታ ውጪ የሆነውን ያደበዝዘዋል። ከዛ በኋላ በመንፈሱ በተከፈተው ቀጭን መስመር ላይ ሲቆም ሌላ አሳብን ማመላለስ እጅግ አዳጋች ይሆናልና ወጣቶች በግፊት በመጣው የመንፈሱ ጤናማ ያልሆነ የግንኙነት ስሜት ተቃጥለው ከተመለከቱ በኋላ ልቦናቸውን #ለጊዜው ለቀቅ ስለሚያደርገው፤ መልሰው በራሳቸው ጊዜያዊ ስሜት ግራ በመጋባት የፊልም ሱሱን ለማቆም ለራሳቸው ከሕሊናቸው የገቡትን ቃል አፍርሰው ደግመው በዝሙት ግብር በመውደቃቸው ይጸጸታሉ። ራሳቸውን የስሜት ተገዢና የፍትወት ምርኮኛ

አድርገው እንዲቆጥሩ መናፍስቱ አሳብ ስለሚያቀርቡ፤ በቁጭትና በንዴት በመብሰክሰክ ከራሳቸው ጋር እንዲጣሉ ስለሚገዷዱ ይሄ ልማድ በሚዷጋገምበት ጊዜ ከፍተኛ የስነልቦና ጭንቀት ይፈጥራል። ይህም ጭንቀት ለዓመታት በሚቀጥልበት ጊዜ ወደሌሎች የአሳብ አመለካከቶችና ማኅበራዊ ግንኙነቶች በቀላሉ በመሻገር ሁሌ ድበታ ያልተለየው፣ ለምንም ነገር ስሜት ያጣና ደንታ ቢስ የሆነ፣ በየቀኑ ድካምና መልፈስፈስ የሚሰማው ሰው እንዲሆን የኑሮ አካሄዱ በመናፍስቱ የጥፋት አካሄድ መሠረት እየተቀረጸ ይሄዳል።

## 2) ብቸኝነት

በመናፍስት እስራት ውስጥ የገባ የወሲብ ፊልም ጥገኝነት ባሕሪያችንን ቀስ በቀስ ቤተሰባዊና ማኅበራዊ ግንኙነቶችን በመቧጠጥና በማሻከር የብቸኝነት ሰዓትን በመጨመር ለሱሱ ብቻ ተገዢ እንድንሆን ያስገድዳል። በተለይ የልማዱን ጥማት ለመወጣት የሚመቸው ለብቻ በመሆን ስለሆነ፤ የብቻ ጊዜያትን በሕይወት ውስጥ በመጨመር በር ዘግቶ ለረጅም ሰዓታት በወሲብ ፊልም ውስጥ ኑሮን በመደበቅ ከመናፍስቱ ጋር ግንኙነት(ግለ-ሩካቤ) በማሰልጠን የግለሰቦችን የዕለት ተዕለት የኑሮ አቅጣጫ ሳያሳውቅ የሚያበላሽ ይሆናል። አንድ *ሥራ* ለመ*ሥ*ራት፣ ጥናት ለማጥናት፣ መጽሐፍ ለማንበብ ስንሞክር የወሲብ ፊልሞቹ ትውስታ በመናፍስቱ ግፊት በኩል ምናብ እየሆኑ የአእምሮአችን ግድግዳ ላይ ስለሚሳሉ፤ የግለ ሩካቤውን ግብር እስከምንፈጽመበትና መንፈሱን እስከምናስደስትበት ደቂቃ ድረስ ይሄ የምናብ ግፊት አይለቅም።

በመሆኑም የጀመርነውን *ሥራ*፣ ጥናት አሊያ ንባብ አቋርጠን የወሲብ ፊልም መመልከት ወይንም በመናፍስቱ እገዛ በኩል ወደ ውስጠኛ የምናበ ክፍላችን በመመሰጥ ያየነውን የወሲብ ምስል ደግመን በሐሊና እያየን የመናፍስቱን ጥያቄ ለመመለስ በመናፍስቱ እንገደዳለን። ይሄም በእግዚአብሔር የአምልኮት ሕይወትና የዘወትር መንፈሳዊ ልምምድ ብቻ የምንዋጋው የጠላት ክንድ ስለመሆኑ መረጃው ብዙ ጊዜ ስለማይኖረን፤ ከልማዱ ግብሩ ከመላቀቅ ይልቅ አብዝተን እየገባንበት ወደ ብቸኝነት አቅጣጫ ሳናስተውል ርቀን በመጓዝ ቤት ስንገባ ብቸኛ፤ ከሰው ጋር ስንሆን ብቸኛ፤ ከቤተሰብ ጋር ስንጨዋወት ብቸኛ እየሆንን ስውር የመናፍስቱን ትዳር አግብተን እንኖራለን ማለት ነው።

## 3) ልቅነት እና ግዴየለሽነት

የወሲብ መናፍስቶች ሌላው በትውልድ የሰው ልጆች ልቦና ላይ የሚያስከትሉት ከፍተኛ ተጽዕኖ መረን የለቀቀ ስድነትና ቸልተኝነት ነው። በዝሙት ፊልምና በግለ ወሲብ ሱስ የተጠመዱ ብዙ ሰዎች ያፈነገጠና ከተፈጥሮአዊው ሁነት የተጣላ የሩካቤ ስሜትና ፍላጎት የሚኖራቸው ሲሆን ማለትም ዓይናውጣነትና ምንም የነውር ስሜት የማይገኝበት የወሲብ ልምምድና አኗኗር በመያዝ የሴሰኝነት ጠባያትን ከአጉል አመል ገጽታ ጋር መላበስ ዕድል ፈንታቸው ነው። በአንፃሩ ደሞ ጭራሽ ከተፈጥሮአዊው ስሜት የተጣረሰ የሩካቤ ፍላጎት መቀዛቀዝ በመከተል፤ ከፊልሞቹና ከግለ እርካታው ልምምድ ውጪ የትዳር አጋርን በመሸሽና በመጥላት በዚህም ሳቢያ የአብራክ ክፋይ ልጅ በማጣት የሌሎችን ሕይወት እያዩ እንዲማረሩና ራሳቸውንም ሆነ ትዳራቸውን እንዲጠሉ መንፈሱ ይገፋፋቸዋል። ይህ ሁኔታ ራስን በራስ እስከመቅጠፍ ደረጃ ሊደርስ ይችላል።

+++

ገና ከመነሻ ዓላማቸውም የወሲብ ፊልሞቹ ሲሠሩና ሲበተኑ ራእያቸው ራሱን፣ ጊዜውንና ኑሮውን የማይገዛ ትውልድን ለመፍጠር ግብ ተደርገው የተለቀቁ ስለሆኑ፤ መናፍስቶቹ የባለቤቶቹን ፍላጎት በተገበረላቸው ጭዳ በኩል ለማሟላት የሚቆራኙትን ግለሰብ ደንታ ቢስ፣ ለእውነትና ለቁም ነገር ቦታ የማይሰጥ፣ ኑሮውን ቀጥ አድርጎ መምራት የማይቸልና ሁልጊዜ መዝናናት የሚያምረው በማድረግ በሁሉም የሕይወቱ አቅጣጫ የማይከናወንለት ከንቱ ያደርጉታል።

+++

በዝሙት መናፍስት የታሰረ ሰው ራእይ፣ ዓላማ፣ ስኬትና የሕይወት የበረከት ውጣ ውረድ በፍጹም አይገቡትም። ስለዚህ ለምንም አይነት አጋጣሚና ዕድል የሚያሳየው ፍላጎትና እቅድ የተዝረከረከ ስለሚሆን፤ ከወሲብ በቀር በምድር ላይ የሚያስደስተው ነገር አይኖርም። በዚህም ባሕሪው በየጊዜው ከነፍሱ ማንነት ጋር ስለሚጋጭ፤ ይህንን ውስጣዊ ፍጭት ለማስታገስ ሁሌ መዝናናት፣ መደሰት፣ ነገሮችን መርሳት፣ በሱስና አደንዣዥ ዕፅ መደበቅ የሚመርጥ ችግሩንም ለይቶ መናገር የማይችልና ቢችልም የሚያሳፍረው የውጭ ሳቂታ የውስጥ አልቃሽ ይሆናል።

+++

ብዙ ወጣቶች በዘመናችን እንደበታቸው በወሲብና ልቅ በሆኑ ቃላት የተጀቦነ፤ በስድብም፣ በነቀፋም፣ በምክርም፣ በውይይትም፣ በጽሑፍ ልውውጥም መካከል የዝሙት ስሜቶችንና ፍላጎቶችን የሚያንጸባርቁ ድምፆችን እያሰሙ፤ የነውር ኃላፊነት የራቃቸው ቋንቋዎችን መናገር የዘመናዊው ባለ ቴክሎኖጂ ትውልድ መገለጫ ሆኗል። የዚህ የስነምግባርና የእምነት እሴት መጨንገፍ ምክንያቱ እነዚህ በህቡዕ ድርጅቶች አማካኝነት የሚሰራጩት የወሲብ ፊልሞች የርኩሰት ውጤት አንደኛው ሲሆን፤ ሰው ያስገባውን የውስጥ መረጃ ወደ ውጪ በሚገልጥበት ጊዜ ያንኑ የተመለከተውን ጸያፍ ድርጊትና የላሸቀ ምግባር ይገልጣል። በዚህም ምክንያት ከአፉ እሳት የሚተፋ፣ ያመጣለትን ቃላት የሚናገር፣ አንደበቱን ከዝሙት ቃላት ማሸሽ የማይችል እና በየሄደበት ቦታ የቀልድና የፌዝ ወሲባዊ ገጽታዎችን የሚያንጸባርቅ የሰይጣን ገጸ ባሕሪይ የሆነ ትውልድ እንዲፈጠር የተዘራው የመናፍስትና የክፉዎች ዘር አፍርቶ በኛም ትውልድ ሁለንተናዊ መጣረስና መፋለስ የሚስተዋልበት የሰው ልጆች ዘመን ይገኝ ዘንድ ተገድደናል።

## 4) መፍዘዝና መደንበኘር

የወሲብ ፊልምን አዘወትሮ የመከታተል ሌላኛው ስነልቦናዊ ጠንቁ፤ መናፍስታዊ አዚም የተጫነው የውስጥ ሕይወት መደንዘዝና ዝምታ በመሆኑ በየቀኑ ከዚህ ስሜት ለመላቀቅ ተጨማሪ ፊልሞችንና ምስሎችን ለማየት የሕሊና አሳብ ግፊት ሲኖር፤ ዘወትር መደብዘዙና መፈዘዙ እየጨመረ የሚሄድ ይሆናል። የወሲብ ፊልም ሱስ የመሆን አቅሙ እንደ ጫት፣ ሲጋራና ሐሺሽ በመሆኑ፤ የሱስ ግብሩን በመናፍስቱ ጫና በኩል በሚጠይቅበት ጊዜ፤ ግብሩ በወቅቱና በሰዓቱ ካልተሰጠው የአእምሮ ዝለትና መዳከምን መናፍስቱ ከውስጥ ይለቃሉ። ልክ በሲጋራ ሱስ መላልሶ እንደሚያፋሽክ ሰው፤ የወሲብ ፊልም ሱስ ያየዘው ልቦናም ደጋግሞ በስሜት ስለሚያፋሽክ የሱስ ግብሩ ርሃብ ካልታገሰለት በቀር ግለሰቡ እረፍት አይሰማውም። በዚያ ቀን እንደምንም ተቋቁሞ ቢያልፍ፤ ወይንም ከሌሎች ሰዎች ጋር በመቆየት ጭንቅላቱን ለማረሳሳት ቢሞክርም፤ በሌላ ቀን አዘናግቶ መልሶ ይህንኑ የአእምሮ ማፋሽክ ስለሚፈጥር፤ ባለፉት 'የአምጣ' ጥያቄ ቀናት ትግል የተዳከመው ሕሊና በሌላ የሚከተለውን የመናፍስቱን ጫና መቋቋም ያቅተውና ይወድቃል። ይሄም የውስጥ ጭንቅላት የኃይል አቅም እጥረትና መልፈዝፈዝ የሚያስከትል ስለሆነ መፍዘዝና መደንገዝ በወሲብ ፊልም መናፍስቶች የተያዙ ሰዎች የሚሰማቸው ማንም የማይረዳላቸው የውስጥ የባሕሪይ እከል ይሆናል።

## ✞ የወሲብ ፊልም የቱን ያህል በዘመኑ ፋሽን ዘልቆ ሄዷ? ✞

የዝሙት ፊልሞችና ምስሎች በዓለም አህጉራት በከፍተኛ ደረጃ የመሰራጨታቸው ሚስጢር ከጀርባው በተቀናጀ አደረጃጀትና ህቡዕ በሆነ አካሄድ ውስጥ የተሰለፉ የሚስጢር ማኅበራት ተጽዕኖ እና አቅም አማካኝነት ነው። አብዛኛው የወጣቱ ትውልድም በቀላሉ በሚያገኘው የእጅ ስልኮቹና የመገናኛ አውታሮች በኩል የሚለቀቁት እነዚህ የርኩሳን መናፍስት አዚማዊ መሣሪያ የሚሆኑ ፊልሞች፤ ወደኑሮና ልማድ የመቀላቀል ፍጥነታቸው ከፍተኛ የሆነ ሲሆን ያለ ውጣ ውረድና ተጨማሪ ጉልበት የተፈጥሮ ስሜት ላይ በመመርኮዝ የአእምሮ ክፍልን ተቆጣጥሮ በፍላጎት ስሜት አነሁልሎ በማደንዘዝ ወደ ልክፍት የሚመራ ስውር የማይነገርለት ጠፍናጊ ሱስ የመሆን ባሕሪይ ያለው የክፍለ ዘመናችን ማፍዝዣና ትውልድን ማሰሪያ ወጥመድ ነው።

+++

ፊልሞቹ በጥንቃቄ ታቅደው ሲዘጋጁ ከኋላቸው እንዲያሳኳቸው የተቀመጡላቸው መናፍስታዊ ራእይና ግብ አላቸው። ከነዚያም መካከል ትውልዱ በሚከተላቸው የፋሽን፣ የአለባበስ፣ የመዝናኛ እና ሌሎች ዘርፎች በኩል ተዘዋዋሪ የሚመስል ነገር ግን በቀጥታ የተቆራኘ ዲያቢሎሳዊ ስብከቶችንና መገለጫዎችን ማስፋፋት አንደኛው ሲሆን፤ በእውነትም ታዲያ በዚህ በኩል ያለውን ግፊትና ያመጣውን ግልጽ ጫና ከትውልዳችንና ዘመኑ ጋር አሰናስለን ስንመለከተው በእጅጉ ተሳክቶላቸው በድሉም ከፍተኛ እርካታንና ድል አድራጊነት የሚያመጣላቸውን ስራ እንደፈጸሙ ማገናዘብ እንችላለን።

+++

እነዚህ የዝሙት ኢንዱስትሪዎች ጥፋት አድራሽነታቸውና የትውልድ ልክፍትነታቸው ገሃድ በወጣ እውነታ ያለ ማስረጃና ሰነድ አስፈላጊነት የተረጋገጠ ሲሆን፤ ነገር ግን "ተዉ" የሚላቸው ጠንካራ የመንግሥትና የግለሰቦች ተቋም እምብዛም አለመኖሩን ስናጤን፤ ከዓለም መንግሥታት ጀርባ ያሉት መናፍስታዊ መዋቅር ያላቸው ድርጅቶች ባለ ጠንካራ ሰንሰለታማ አሳሪዎቹ የሚስጢር ማኅበራት ከንድ የቱን ያህል እግዚአብሔር በረሳ ትውልድና ዘመን ላይ በርትቶ እየደቆሰ፣ እየጠመዘዘና እየገፈተረ እንዳለ መረዳት ያስችለናል። የወሲብ ፊልሞች አደገኝነት በንጽጽር ሲታይ ጥቂት የሚሆኑ ተመራማሪዎችና አጥኚዎች ጉዳቱንና ሁሉ ገብ አከሉን በሰዎች ቋሚ ምስክርነት እያረጋገጡ ትምህርትና መረጃ ቢሰጡበትም፤ የወሲብ ኢንዱስትሪዎቹ ከተሰራጩበት ጥልቀትና ስፋት አንፃር፤ እንዲሁ ትውልዱ ውስጥ ሥር ሰደው ካሉት የመናፍስት አገዛዝና አሠራር ምክንያት በቀላሉ ለኃጢአትና ለእርግማን አሳቦችና ድርጊቶች የመሳብ አዝማሚያው ከፍተኛ በመሆኑ፤ እዚህ ግባ የማይባል ለውጥ ሳያመጡ ቀርቶዋል።

## ✞ የወሲብ ኢንዱስትሪና የፋሽን ኢንዱስትሪ ጣምራ ሂደት ✞

ከላይ በተገለጸው መልኩ እንደተቀመጠው ጉልህ የሆነና በቁጥርም የበዛ ጥናትና ምርምር ባለመካሄዱ እንጂ በዛሬው ትውልድ እውነታ ውስጥ የዝሙት ኢንዱስትሪ ተቋማት የአሻራ ተጽዕኖ ያልነካካው የሕይወት ዘርፍ ፈልጎ ማግኘት የሚያዳግት ይሆናል። ከነዚህ በታላቅ ተጽዕኖ ውስጥ ውድቀው በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የሚስጢር ማኅበራቱ ተልዕኮና እቅድ ተፈጻሚ ከሆነባቸው የትውልዱ ገጽታዎች መካከል የፋሽን ኢንዱስትሪው ይጠቀሳል።

+++

ዛሬ በፋሽን ኢንዱስትሪው በኩል በየቀኑ እየተመረቱ የሚወጡት የልብስ ቅርጾችና ይዘቶች፣ የመዋቢያ መሳሪያዎች፣ የተለያዩ ቁሳቁሶች በአብዛኛው ራቁት ገላን የሚያበረታቱና ዝሙት ነክ እንድምታ የሚነበብባቸው ናቸው። ርጉማን መናፍስት፤ የዘመኑን ትውልድ የቀልብ አሳብ አዎንታዊ በሚመስል ስሜት አነሁልሎ በራቁትነት ገጽታ በመሳብ፤ የፋሽንና የአለባበስ ሴሰኝነትን የሚያንጸባርቅ ፍላጎት በመፍጠር፤ በዓይን በመመልከት ብቻ የሕሊናን እምነት መስመር በማሳት፤ ውስጣዊ ዝንባሌን ከመናፍስት ትዕዛዝ በሚመነጭ ግፊት በማስቀልበስ ወሲብ ናፋቂ እንዲኮን ያደርጋሉ።

ዘመናት አስቀድሞ አጭር ቀሚስና ደረት የሚገለብጥ ልብስ መልበስ በተለይ በኛ ማኅበረሰብ እሴትና እይታ መሠረት ነውር የተባለ ሲሆን፤ ዛሬ ነውሩ ረጃጅም ቀሚስ መልበስ እንደሆነ ሁሉ ከተማና ፈረንጅ ቀመስ የኑሮ ዘልማዶቻችን ውስጥ የአእምሮ መፍዘዝን በመናፍስቱ አስገዳጅነት አስቀምጠውብን ራቁትነትን እንደ ባሕል ለውጥ አጸደቅነው፤ 'እሴትን' የዘመን ያለፈ ታሪክ 'ነውርን' የዘመን ነባራዊ እውነት ለማድረግ ተገድደናል። በዚህ ጊዜ የሚመረቱትም ልብሶች በብዛት ሆነ ብለው ሙታንታ ላለመሆን ሩብ የቀራቸው ቀሚሶችና አልባሳት ላይ በጣም ያተኮሩ ስለሆኑ፤ ይህንን እንቃወማለን አሊያም አንለብስም የሚሉ ሴቶች እስኪቸገሩ ድረስ ዘመኑ እንደጠቅላላ አጋድሎ ራሱ አስገዳጅ ራሱ ፈራጅ የሆነ ትውልድን ሲያፈራ ከጀርባ ያሉት የመናፍስት ማኅበራት በእጅጉ ረክተውና በግባቸው መሳካትም ተደስተው፤ ዝሙት ዝሙት የሚሸት ኑሮን ከተለያየ አቅጣጫ ለጊዜው ሲያሠለጥኑ እኛ ቢቸገር ነንና ተራ በተራ እስከምንጨነቅ ድረስ፤ ተራ በተራ እስከምንሰቃይ ድረስ ቶሎ አይገባንም። ቢገባንም ዘመኑንና ትውልዱ እንደሆነው ለመሆን እንጂ የእምነትንና የማኅበረሰብን የእውነት ኃይል ለማስጠበቅ ሰብረን የምናልፍበት እውነቱም፣ ድፍረቱም፣ ፍላጎቱም የለንም።

+++

በመናፍስታዊ ቁራኝነት ተለውሰው የሚለቀቁት የዝሙት ፊልሞችና ምስሎች በብዛት ሴቶችን እንደ ፍትወት ስሜት ማስታገሻ የቆጠሩና ተፈጥሮ ሁነታቸውንም ያከበሩ ስላይደሉ፤ ይህንኑ የመርዝ ዲያቢሎሳዊ ፕሮፖ-ጋንዳ በአልባስና በጌጣጌጥ በኩል እየለወሱት ለትውልዱ ልቦና መጋሸብና መጥፋት መንስኤ ሆነው፤ ሴት ልጆች በአጭር ቀሚስና ቁምጣ፣ ደረት በሚገለብጥ ልብስና ተክለ ሰውነትን በጉልህ በሚያሳይ ፋሽን እንዲያጌጡ የማስገደድ ያህል በስውር እየተጫኑ፤ በዚህኛው በኩል ደግሞ ይመጡና የውበት መለኪያና ደረጃ ራሳቸው ሆነው፤ ያልተራቆተች፣ ዘመኑን ያልመሰለችና ያልተጋጌጠች እንስት ከውበት መለኪያው በታች እንደሆነች፣ በተቃራኒ ጾታ ተመራጭነት ደረጃ ውስጥ ያልተካተተች፣ ኋላ ቀር እንደሆነች፣ ዘመኑን መዋጀት የተሣናትና የኢኮኖሚ ጥገኛ የሆነች እንደሆነች አድርገው በሙዚቃው፣ በፊልሙ፣ በመጽሐፍቱና በመዝናኛ ሚዲያው በኩል ይደሰኩራሉ።

ገንዘብንና የሚዲያ አውታሮችን በመቆጣጠሩ ረገድ ከፍተኛ ሚና እና ኃይል ያላቸው እነዚህ የዲያቢሎስ እጆች የሆኑት ህቡዕ ድርጅቶች፤ የተራቆተ ልብስና ዘመኑን የሚመስል ልብስ ለመልበስ የሚፈልጉ ቆነጃጅት

እንስቶቸን እየመረጡ በየፊልምና መዙቃው ኢንዷስትሪው የፊት ገጽነትን ሽፋን እየሰጡ፤ የዜናዎቸንና የመገናኛ ሚዲያ አትኩሮት አቅጣጫዎቸን ቀድመው እየቀየሱ፤ በኢኮኖሚና የዝና ደረጃ እየደገፉ ወዷላይ ወዷ አርአያነት ደረጃ እንዲወጡ  ከተደረገ በኋላ፤ ትውልዱን በነዚህ አርቲስቶችና የሚዲያ ሰዎች በኩል ስቦ መምራት ብዙም የማይቸግር ሆኖላቸዋል። ካለፉት መቶ ዓመታት ወዲህ በሚያስደነግጥ በከፍተኛ ፍጥነትና ተደራሽነት ወዷ ዓለም የተሰራጩት የወሲብ ፊልሞችም የዓለሙን ዘመናዊ ትውልድ የሰብዓዊነት ቅርጽ ከነሥነ ምግባር ገጽታው ከውስጥ በመናፍስት ዳፍንታዊ አገዛዝ ስልት በኩል ስለተቆጣጠሩ፤ በእውነት ያለበሱትን የሚለብስ ትውልድ መገኘቱ ምንም የሚያስገርም አይሆንም።
" <u>ሴቲቱም በቀይና በሐምራዊ ልብስ ተጐናጽፋ በወርቅና በከበሩ ድንጋዮች በዕንቈቾም ተሸልማ ነበር፥ በእጅዋም የሚያስጸይፍ ነገር የዝሙትዋም ርኵሰት የሞላባትን የወርቅ ጽዋ ያዘቸ፤</u>"
(የዮሐንስ ራእይ 17፥4)

የወሲብ ፊልሞቸና የዘመኑ የፋሽን ገጽታዎቸ አይገናኙም ብሎ ማሰብ የበዛ የዋህነት ነው። ምክንያቱም የዝሙት ኢንዷስትሪዎቸ ከዘመን ዘመን አቅማቸውና ብዛታቸው እየጨመረ በመጣበት ልክ፤ በተመሳሳይ የፋሽን ኢንዷስትሪውም የሚያንጸባርቃቸው የምርት ውጤቶቸና ገጽታዎቸ እጅግ በብዛት ወሲብ ነክ መሆኑ ግልጽ ምርምር የማያሻ ማስረጃው ነው። የወሲብ ፊልም ኢንዷስትሪውና የፋሽን ኢንዷስትሪው በጣምራ ሂደት በስኬት ሲጓዙና እንዲጓዙም በጎን የዝሙትን ትኩሳት የሚወክል እንቅስቃሴና ትርክት በቀልድ እያዋዙ በመዝናኛ ሚዲያዎቸ በኩል የሰዎቸን ቀልብ በማነሣሣት፤ ትውልዱ በዝሙት ምኞት በእጅጉ እንዲጠመድ የተቀናበረ ሴራ በመሆኑ፤ በመናፍስት የደነዘዘ ትውልድ፤ ራቁት ሲለበስ ደስ ይለዋል እንጂ አይከፋውም። ስለዚህ ከዘመን ዘመን የምትመጣው የቀሚሷና የቁምጣዋ ዲዛይን የቱን ያህል ገላን ብትገልጥ ተቃውሞ እንደማይገጥማት ዘመኑን በማጤን ብቻ መገነዘብ ይቻላል።
" <u>ያየሃትም ሴት በምድር ነገሥታት ላይ የምትነግሥ ታላቂቱ ከተማ ናት</u>።"
(የዮሐንስ ራእይ 17፥18)

+++

ወዷኛም አገር ስንመጣ፤ የፋሽን የዘመን ልብሶቸና የማጌጫ መንገዶቸን ከነአተላው ከምዕራባዊያን የተቀበለው ትውልዳቸን፤ አሁን ላይ ረጅም ርቀትን ተጉዞ መረን አልባነትን በፋሽን ዘመናዊነት ማዕቀፍ ሥር በጥምዘዛ ተቀብሎት በጊዜያትም ውስጥ እንዷራሱ አንፃራዊ ገጽታ አስተናግዶት ለምዶት መጥቶ፤ አሁን ብዙ ሐሰቶቸ መካከል አንድ እውነት ዋጋ እንዷሌላት በምትቆጠርበት የመስማማት ሂደት ላይ ደርሰን "ኸረ ተዉ እንደርሱ አይደለም!" ለማለትም አስቸጋሪ ሆነ። በመሆኑም ዘመናት በጨመሩ ቁጥር እህቶቻቸንን ልብስ እየቀነሱ ተቸግረው አስቸገሩ። ወንድሞቻቸንም እንዷው ዘመኑን መስላ የምትታይ ሴትን ለማድነቅ እጅ ስልካቸው ላይ የተሰገሰገው የዝሙት መዝናኛ አዚም እና ጫና ስላለባቸው አራድነት በመሰላቸው እይታ ገለጥለጥ ላለቺው እያጨበጨቡ፤ ሸፍነፍን ያለቺውን እየፎገሩ የዝሙትዋን ንግሥት መንፈስ እያገዙ ስንት ዘመን መጡ?

+++

የፋሽን ኢንዷስትሪዎቹን በተመሳሳይ መልኩ ከዝሙት መናፍስት ጋራ በማቆራኘት፤ እርቃን እይታን በመፍጠር የስሜትን ገጽ መንዳት የሚቸሉ ቡዳዎቸን ልክፍት በማድረግ፤ የአስተሳሰብ ጠለልን ወዷ ሥጋዊ ፍቃድ ብቻ እንዲያዘነብል በመቀየስ፤ የውበት አድናቂነት የሚመስል የሩካቤ ምኞትን በማንገሥ፤ የዝሙት ተነሣሽነትን እንደ ልዩ ደስታ በመቁጠር፤ የመንፈስ መሳሳብን እንደ ጤናማ ግንኙነት በማስመሰል የሚፈጸመው የአጥማጅነት መረብ በብዙ መንገድ ላይ ተሳክቶለት የተራቆተ ዘመን፣ የተራቆተ ትውልድ፣ የተራቆተ ሕሊናና የእምነት ኃይል እንዲኖር ጊዜው ተፈርዶበታል።

+++

የሚስጢር ማኅበራቱ በዚሁ በፋሽንና በጌጣጌጡ ኢንዷስትሪ በኩል ትውልዱን በአሻጥር መናፍስታዊ የእጅ አዙር ቀኝ ግዛት መንገድ ላይ ለማቆም የቻሉበት መርሃቸው 'ሰው የፈለገውን የመከተል መብት አለው!' የሚል ነፃነትንና አማራጭን የሚከፍት የሚመስል ነገር ግን የውዴታ ግዴታ ተገዢ የሚያደርግ አሠራር ያለበት ወጥመድ በመዘርጋታቸው ነው። ስለሆነም ትውልዱ 'ሰው የፈለገውን የመልበስ መብት አለው፣ ካሻው ራቁቱንም ይሂድ፣ እኩልነት ሰው የፈለገውን እንዲያደርግ መተው ነው' የሚል አመለካከቶቸን እንዲይዝ በታቀደለት መርብ ውስጥ ገብቶ ሲያበቃ  ልምከርህ፤ ቆይ ላርምህ ብትለው ነፃነቱን እየነጠቀውና ከሥልጣኔ ዘመንም እያወጣኸው ይመስለዋል።

<< ሰው የፈለገውን የመከተል መብት አለው! >> የሚለው የመመሪያ መፈክር(Slogan) ጀርባ ያለው የሚስጢር ማኅበራቱ አሳብ ምንድነው?

☞ እግዚአብሔር አምላክ በግድ የሚገዛና የሰው ልጆችን ነፃነት የሚያፍን አምባገንን አድርጎ ትውልዱን በፍልስፍናና ቲዎሪዎች በኩል ማሳመን
☞ የሰው ልጅ ከፈለገ ከሰይጣንም ጋር መግባባትና ለጋራ ሕልውና መሥራት ይችላል የሚል መናፍስታዊ አገዛዎችን ማሰልጠን
☞ የፈለከውን ተከተል በሚል የምርጫዎች ክፍተት ውስጥ ዲያቢሎሳዊ አማራጮችን በመሰግሰግና በማብዛት የአስተሳሰብን አድማስ ወደግራ ግራው እንዲያዘንብል አቅጣጫ መቀየስ
☞ በሃይማኖትና በእውነታ መስመሮች በኩል ያሉትን የሰው ልጆችን መርሆች ከሰብአዊነት የተፈጥሮ ሕገ ልቦና ጋራ መሻርና መጣስ ደስታ የሚሰጥ ብሎም ነፃነትን የሚያጎናጽፍ እንደሆነ አድርጎ በተለያዩ መንገዶች በማሳየት የአዋቂነትና የመዘመን መግለጫ ሚዛን ውስጥ ደረጃ አሊያም ልኬት ማስቀመጥ
☞ ትውልዱን "አንተ ለራስህ አዋቂ ነህ" በሚል የማፍዝዣ ፖሮፖ ጋንዳ በማጥመቅ፤ ደጉንና ክፉውን በአእምሮና ልቦና ውስጥ ብቻ እንዲያውቃቸው የይስሙላ ትምህርት በመስጠት መሬት ላይ የሚወርደውና የሚተገበረው የርዮተ ዓለም ትምህርት፣ ጽንሰ ሐሳብ፣ ፍልስፍና እና የግኝቶች አስተንትኖት ክፋትን በተሸፋፈነ ሴራ የሚያስፈጽሙ እየሆኑና ገሚስ ደግነትን ለታይታ እንዲያሳዩ እየተደረጉ፤ መልካምና ደግ ነገራት ከአእምሮና ልቦና ውስጥ የማይወለጹና የቀሩ ሐሳቦች እያደረጉ ማጨንገፍ

+++

ወገኖቼ የክርስቲያን ልብስ ምንድነው? " <u>ነገር ግን ጌታን ኢየሱስ ክርስቶስን ልበሱት፤ ምኞቱንም እንዲፈጽም ለሥጋ አታስቡ።</u>
"  ነው የሚለው ወደ ሮሜ ሰዎች 13፥14 ላይ። ክርስቶስ የጸድቅ ልብሳችን ነው። ሥጋና ደሙን በምድር ተቶልን የሄደው እንደ ልብስ እናጠልቃቸው ዘንድ ነው። በውስጣችን እርሱ ይኖር ዘንድ ነው። አኛ በእርሱ እንኖር ዘንድ ነው።
ዛሬ ክርስቲያኑ ምን ይለብሳል? አንገቱ ላይ መስቀል ያነገተው እንዴት ነው ገጽታው? በዚህ በዚህ ሙሲልም እህቶቻችን በንጽጽር የተሻሉ ኃበዞች ናቸው። በአብዛኛው ሃይማኖታቸውን ከሚወክል ታይታ ውጪ አይገለጹም። እንደው ዘመናዊ እንሁን ቢሉ እንኳ አጠማጠሟን እንደሚያደርጉ ያደርጓታል እንጂ የወጣ ነገር አይታይባቸውም። መስቀል ያደረገነውስ?

+++

እንግዲህ ፋሽንና አለባበስ ላይ ርዕስ ስናነሣ ዋናው ተዋናዮች እህቶቻችን ናቸው።
እስኪ እንዴት ነው ወጣት ሴቶች ምን ታስባላችሁ? አሁን ይሄን የአለባበስ ጉዳይ ከሕግ አንፃር ሲነገረን ማምለጫው እንጂ ማመኛው ላይ መንገድ አንፈልግም። ለዚህ ነው ደጋግሜ የሃይማኖት ጉዞ መነሻ የእግዚአብሔር ፍቅር መሆን አለበት የምለው። እስኪ ስለ ሁኔታው ከነፍሳችሁ ጋር አውሩበት። በአለባበስ ሁኔታችን አባት የሆነን እግዚአብሔር አምላክ ምን ይሰማዋል? ብለን ነፍሳችንን ስናወራ ምን ይሰማናል? ነገሩ ከውስጥ ካልቆረቆረን ከላይ ተደጋግሞ ብንሰበክም፣ ብንመከርም፣ ብንዘከርም አስቸጋሪ ነው። ስለዚህ እህቶቻችን እስኪ ትንፋሽ ውሰዱና አስቡበት። እውነቴን ነው የምላችሁ ውበት ሃይማኖት ነው።
በዘመናዊነት ጫና መካከል የወደቃችሁ ወጣቶች ሁሉ በደንብ ልታስቡበት ይገባል። እናንተ የግዜዎች አይደላችሁም። ግዜ ሲበርደው የሚበርዳችሁ፣ ግዜ ሲሞቀው የሚሞቃችሁ፣ ግዜ ሲራቆት የምትራቆቱ፣ ግዜ ሲከናነብ የምትከናነቡ፣ ግዜ ሲደነግጥ የምትደነግጡ፣ ግዜ ሲረጋጋ የምትረጋጉ መሆን የለባችሁም። ዘላለማዊነት ከውስጣችሁ እንዳይወጣ ዕለት ተዕለት ገዜያችሁን በአምልኮተ እግዚአብሔር እየባረካችሁ እና በቅዱስ ቁርባን ውስጥ ዘመናችሁን አሳርፉት እንጂ እንደ ዘመኑ አትሁኑ።

(ወደ ኤፌሶን ሰዎች ምዕ. 5)
------
<u>15፤ እንግዲህ እንደ ጥበበኞች እንጂ ጥበብ እንደሌላቸው ሳይሆን እንዴት እንድትመላለሱ በጥንቃቄ ተጠበቁ፤</u>
<u>16፤ ቀኖቹ ክፉዎች ናቸውና ዘመኑን ዋጁ።</u>
<u>17፤ ስለዚህ የጌታ ፈቃድ ምን እንደ ሆነ አስተውሉ እንጂ ሞኞች አትሁኑ።</u>

## ✞ የወሲብ ፊልምና የመዝናኛው ኢንዱስትሪ ተያያዥነት ✞

በክፍል ሦስት ትምህርታችን ለማንሣት እንደተሞከረው "የወሲብ ፊልሞችና የፋሽን ኢንዱስትሪ በጣምራ እንዲጓዙ" የአያያዥነቱን ሚና መሣሪያ ሆኖ የተጫወተው የመዝናኛው ኢንዱስትሪው ነው። አሁን እንዴት ማለት ነው፤ አንድ በሦስት ፈረሶች የሚጎተት ጋሪ ላይ ተቀምጦ የሚንቀሳቀሰን ሰው አስቡ፡ ግለሰቡ ፈረሶቹን ወደሚፈልግበት አቅጣጫ መንገድ በማስያዝ መሪ እየሆነ ወዳሻው ቦታ ይጓዛል። እንዲሁ ደግሞ ሦስቱን ኢንዱስትሪዎች ማለትም የወሲብ ፊልሞችን ኢንዱስትሪ፣ የፋሽን ኢንዱስትሪ እና የመዝናኛ ኢንዱስትሪን በጋራ አያይዞ በመጠቀም የመናፍስት ማኅበራቱ ትውልዱን ወደሚፈልጉበት አኗኗር፣ ሁኔታና የዘመን ገጽታ ለመምራት ችለውበታል። በዚህ አካሄድ ላይ ዲያቢሎሳዊ ቀኝቶችን እንደ ዓለም ትውልድ በሚገባ አስርጾ ለማስፈን እና የሚፈልጉት የዘመን ትውልድና የሕይወት ዘይቤ እንዲከሰት የሚከተሉትን ስልቶች ተጠቅመዋል።

☞ የሥልጣኔ ዘውጎችን ጤናማ የውስጥ ትርጉማቸውን በማፋለስ፤ የሰው ልጅ ከተፈጠረበት መነሻ ዓላማ

ኪሎ ሜትሮችን ርቆ አፍታ ቆም ብሎ ሳያገናዝብ እንዲጎዝ የዓለም ሩጫዎችን መድረሻ ግብ የሥጋ መሠረታዊ ፍላጎቶችን ማሟላት እንደሆነ ብቻ ስለማሳመን ሲሉ፤ በዘርፈ ብዙ ማኅበራዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ታሪካዊና ነባራዊ ስዕሎች ውስጥ የሚፈልጉትን አድምቀው በተደጋጋሚ እያሳዩ በመሳብ፤ ተረግግቶ የዓለም ነገራትን የመፈተሻ ጊዜን እያሳጡ የነፍስ ጥያቄዎችና የሃይማኖት እንድምታዎች የሚጨፈለቁበት ስርዓት መዘርጋት

☞ የሰው ልጆች ሰብአዊ ማንነታቸውን እስኪዘነጉ ድረስ ሌት ተቀን ለሥጋዊ ፍቃዶች ብቻ እንዲሮጡ

ዓለምን እንደ ውድድር መድረክ አድርጎ በመቅረጽ፤ መሠረታዊ የእምነት መደንግጎች የሆኑት ፍቅርን፣ እምነትንና ተስፋን በተለያየ ዘዴ በመጉዳት፤ በምትኩ ጉልበት፣ ውበት፣ ገንዘብ፣ ዝና እና ሥልጣን የመኖር መጀመሪያም መጨረሻም ማረፊያ ተልዕኮዎች እንደሆኑ አስመስሎ የሕይወትን ቀርጽ በሥጋዊ አተረጓጎም ውስጥ ብቻ ለክቶ፤ የእምነትንና የባሕልን እሴቶች በየዘመኑ መድምሰስ

☞ የሕሊና፣ የልቦና እና የነፍስ ሰማያዊ ፍቃዶች በተፈጥሮም በሥጋ ስሜቶች የተከለሉ በመሆናቸው፤

እነዚህ መንፈሳዊ ፍቃዶች ወደ ውጪ እንዳይገለጡና ሥጋን እንዳይገዙ ለመቆጣጠር፤ የሥጋ ምኞቶችን የሚያገዝፉ እንዲሁም የሚያስጠብቁ የተብለጨለጩ ስብከቶችን እና ሽልማቶችን ከፊት እያስቀደሙ በማስቀመጥ፤ ፍላጎቶች ሁሉ ተመሳሳይ የሥጋ ዝንባሌ እንዲንጸባረቅባቸው መናፍስታዊ አዚሞችን በመጠቀም የትውልድን የጊዜ መስመር ከመነሻው፣ ከመካከሉ እና ከመድረሻውም ላይ እየሆኑ መቆጣጠር

☞ የሃይማኖትን ኃይልና መንገድ እንደ ጭቆና ቆጥሮ በማስቆጠር፤ የእምነት አካሄዶች የነጻነት ብዝበዛ

ተጽዕኖ አሳዳሪዎች እንደሆኑ በተለያዩ ቀጥተኛና ተዘዋዋሪ ገለጻዎች ለዓለም በማድረስ፤ ለታሪካዊ ብሎም ለነባራዊ የሕብረተሰብ ችግሮች መንስኤ ናቸው በማለት ተጠያቂነትን ከፈጠሩ በኋላ፤ የሃይማኖት ፋይዳዎችና ጉዞዎችን ማቃለል፣ ማሳደድና ማጥፋት

☞ የፋሽን አልባሳትንና የአካል ተክለ ቁመና ውበትን በፉክክር መልኩ በማቅረብ፤ መገላለጥና መራቆት

እንዲሁም የተዛነፈ አለባበስንና ገጽታን መጠቀም እንደ ልዩ የዘመናዊነት መታያ አድርጎ፤ እርቃንን እንደ ትልቅ ጀብዱና ዝና በመቁጠር፤ ለኃጢአት ማደግና ለመቀሰፍት መብዛት ምክንያት መሆኑን ሰው እንዳይረዳ አድርጎ ትውልዱን የፋሽን ምርኮኛ ማድረግ

☞ የማኅበራዊ ድረገጾችን፣ የመገናኛ አውታሮችን፣ የፊልም እና የሙዚቃ ኢንዱስትሪዎችን ከሥር

ከመሠረቱ በመቆጣጠር፤ በሰዎች ውስጥ ያሉትን መናፍስት ለክፋት አንድነት እንዲተባበሩ የማቀናጃያ ትስስሮሾችን በማመቻቸት፤ ርኩሰት እንዲያይል፣ አመፃ እንዲስፋፋ፣ እርግማን እንዲጸና፣ ሐሰት እንዲበራከት፣ እምነት እንዲሰናከል የማዳከሚያ ዕድሎችን በመጨመር ዘመኑን ከነፍስ ወከፍ አንስቶ በሰይጣናዊ አገዛዝ ሥር መጣል

☞ የሰው ልጆች በአእምሮ አመዛዛኝነትና በሕሊና ፍረደኛነት ነገሮችን እንዳያስተውሉ ስሜታዊነትን እንደ

ደስታ መሸመቻ እንዲሁም ማንጸባረቂያነት በማድረግ፤ አስፈላጊ የኑሮ ግንኙነቶችንና ግንባታዎችን በአጥፊ መናፍስት መሪነት ሥር የወደቁ አጋጣሚ የሚመስሉ ሁነቶች ላይ እንዲጀምራቸው የተለያዩ የፌዝ፣ የቲያሪና የፍልስፍና ጽንሰ ሐሳቦችን በመዝናኛ ማዕከላት በኩል በገፍ በማሰራጨት፤ አጢኖ

የማስተዋልንና የሚመጣውን አሻግሮ የመመርመርን መንፈሳዊ ኃይል በማድከም፤ ስለቅርብ ቅርቡ ክስተቶች ብቻ እንዲኖሩ በውጪያዊ ግፊት ውስጥን ማጨለም

+++

ዓለምን በአንድ ማዕከላዊነት ለመጠቅለል ከሚያገለግሉ ታላላቅ መሣሪያዎች መካከል አንደኛው የሆነው የመዝናኛው ኢንዱስትሪ፣ በተለይም ዛሬ ዛሬ ተጽዕኖው እጅግ ሥር የሰደደና የአጥፊዎቹን የርኩሰት ኃይሎች ለጥፋት የሚውልን ድካም ያቀለለ፤ በአያያዥ ሰፊ አድማስነቱ በኩልም ብዙ የኃጢአት ሥራዎችን እንዲያከናውኑ መንገድ የሆነ ተቋም መሆንን ችሏል።

በዛሬይቱ ዘመን ላይ ደግሞ የመዝናኛ ኢንዱስትሪዎች ጫናና ስርጭት በብዙ የአኗኗር አቀጣጫዎች ላይ ተገኝቶ የአሁኑን ትውልድ ጉዞ መሪ መሆን የቻለ፤ በአቋሙ ግንባታ ውስጥም ሰርጎ ገብቶ ወደ ውጪያዊ ገጽታ ሊያውም እንደሚያኮራ ሆኖ እየተገለጠ ያለ፤ በቋንቋና ማንነት ላይም የራሱን አሻራ ያለ ብዙ አድካሚ ውጣ ውረድ ማኖር የቻለ በመሆኑ፤ ይህንን ተከትሎ የዘመኑ ወጣቶች ኑሮና ሕይወት ምን መልክ ያዘ ስንል የሚከተሉትን እናገኛለን።

❖ በሚታየው የመዝናኛ ኢንዱስትሪ ውስጥ ባሉት የፊት ገጽ አርቲስቶችና ፊት አውራሪዎች አማካኝነት የሚሰጠውን የንግግር፣ የአለባበስና የአኗኗር ልማዶችን ሳይጨምር ሳይቀንስ ወደራሱ ማንነት ያንጸባረቀ ሲሆን ታዲያ፤ አሁን አርቲስቶቹ ሲንጨባረሩ ትውልዳችንም ይንጨባረራል፣ ጠምዛዦቹ ሲራቁቱ ትውልዳችንም ይራቆታል፣ ፊት አውራሪዎቹ ሰላምታቸው ስድብ አዘል ሲሆን እዚህም እኛም ጋር ጸያፍ ቃላት "ደህና አደርክ?"ን ተክተዋል።

❖ አብዛኛዎቹ በመዝናኛው ማዕከላት የሚንጸባረቁት የታይታ ገጽታዎች ሥጋዊ ምኞቶችን የሚያሳዩና ነጻነት መሰል መረን የለቀቁ አንዳንዴም ግልጽ እብደቶችን የሚወክሉ ናቸውና፤ ትውልዳችንም ይህንን የሥጋ ምኞት ለመቀዳጀትና በእንጀራ ብቻ የተመሠረተ ኑሮን ለመገንባት ሲል እርስ በእርሱ በዘመናዊነት ልኬት የሚወዳደር፣ በኢኮኖሚ ደረጃዎች ለመበላለጥ የሚውተረተር፣ ከፊት ፊት ቀድሞ ለመታየት በሚደረገው ጥረት ውስጥ እርስ በእርሱ ከውስጥ የተገፋፋ፤ አንድነትና መተባበር የራቀው ዜጋ ሆነና ቁጭ አለ።

❖ በተጨማሪ ሃይማኖታዊ እውነታዎችን፣ አገረሰባዊ ባሕሎችንና ቤተሰባዊ መስተጋብሮችን የሚንቅ፤ በሥልጡንነት ጓዳና ላይ ለመጓዝ የእምነት ጫናዎችን እንደ ኃታቾ ተጽዕኖ የሚቆጥር፤ ወደፊት መሄድ ማለት የኋላውን መናድና በእርሱ ቦታ አዲሱን ተክቶ መራመድ የሚመስለው፤ ነገራትን ሁሉ ከሥጋ ፍቃድና ዓይን ብቻ የሚለካ፣ ግራ ግብት ያለው፣ መንፈሳዊ ሞገሱን የማያውቅ፣ ጸጋና ራእዩን ያጣ፣ የአባቶቹን የታሪክ ፈለግ ማግኘት የተሣነው፣ ለውሳኔ የሚቸገርና ሁልጊዜ የድካም ስሜት ያልተለየው ትውልድ ሆነን፤ እንዳደረጉን የምንሆን መሞከሪያ አሻንጉሊቶች በመሆን ሰማያዊ ኃይል ርቆን እንባተታለን።

## ✞ የመዝናኘው ኢንዱስትሪና የወሲባዊ ፊልሞች ኢንዱስትሪ ተደጋጋፊነት ✞

የእነዚህ ሁለቱ ኢንዱስትሪዎች የመጀመሪያው የመጣመሪያ አሪቡናቸው፣ ሁለቱም የመዝናኛ አውታር ተቋማት ተደርገው እንዲታሰቡ በተደረጉበት መተሳሰሪያው ላይ ነው። እግዚአብሔር አምላክ ለምድር ፍጥረታት ባርኮና ቀድሶ የሰጠው የጾታ ግንኙነት፤ ዛሬ በተገኘንበት ዘመን ራሱን የቻለ የርኩሰት መዝናኛ ሊሆን ችሏል። በአዳምና ሔዋን በኩል የተሰጠው የቡራኬ ኃይል፣ በአጥፉ መናፍስቶች አማካኝነት በአመንዝራነት ጎኑ የተተረጎመ በመሆኑ፤ ከብዙ ሰዎች ጋር ግንኙነት መፈጸም እንደ ብዙ መዝናናት የታየ ሆኖ ለክፋት ሠራዊት የእርግማን መግለጫ የሚሆን የዝሙት ድሪቶን ዘመኑ ተከናንቦ ቁጭ ብሏል።

+++

የወሲብ ፊልሞች ጥገኛነት እንዲጨምር የፋሽን ኢንዱስትሪዎች የማርገብገቢያውን የውጪ ገጽታ የቡዳ መናፍስትን እያዋረሱ ምርቶችን ሲያቀርቡ፤ ኃትቶ የማምጫውን ሥራ ደግሞ የስብከቱን ክፍል የሚያከናውነው የመዝናኛው ማዕከል ነው።
ካለፉት 100 ዓመታት ወዲህ የይዘታቸው ቅርጽና ሁኔታ ወሲባዊ ቃናዎችን የሚይይዝ የፊልም፣ የሙዚቃና የተለያዩ የመድረክ ዝግጅቶች ተስፋፍተው መጥተዋል። ግለሰቦች በዝሙት ፊልሞች ማዕበል ሰምጠው ባይገኙ እንኳን፤ በነዚህ የመዝናኛ ዘርፎች በኩል "አልሸሹም ዘወር አሉ" የሚያሰኙ ሩካቤያዊ ገጽታዎች፣ ራቁት መልኮች፣ ወሲባዊ ትዕይንቶችና ቃላቶች፣ የስሜት ንዳድን የሚፈጥሩ ታሪኮችና ምልክቶች እየተዘጋጁ ስለሚተላለፉ፤ የወጣቱና የጎልማሳው ክፍለ ዘመን ትውልድ የሆነው የዛሬ ዘመን፣ በሚለቀቁት

የመዝናኛ መልዕክቶች አቅሉን ስቶ ሲገኝ፣ አሁን አሁን በቃ ወሲባዊ ጉዳዮች የማይነሡበት የኑሮ ዘርፍ እየቀነሰ መጣ።

+++

የኛም አገር የጋሸበው ትውልድ በዘመናዊነት ካባ ተጀቡኖ አድርግ የተባለው የሥልጡንነት ፍቃዶች በውዴታ ግዴታ ከገባበት በኋላ አሁን ግዴታው ውዴታ ሆኖበት ይሰቃያል። እዚህም በኛም አገር የሚለቀቁ የመዝናኛ መልዕክቶች ከጊዜያት በኋላ ልክ እንደፈረንጆቹ ለመሆን በብዙ የደከመ ሲሆን፤ አንዳች ዝሙታዊ ምልክት አሊያ ገጽታ መጠቀም ልክ ወጥ ውስጥ እንደሚቀላቀል ማጣፈጫ ጨው የግዴታ አስፈላጊ መስሎ እስከተቀረጸበት ጥጉ ድረስ ግራ ዘመም ሆነን ስንገኝ ያው ቢቸግር ነንና አይገባንም።

+++

ወጣቶች በልጅነት ጊዜያቸው በዐርባና በሰማንያ የተጠመቁት የጥምቀት የሙሽራነት ልብስ ለዕድሜ ዘመን ተከትሎ የሚቆይ በመሆኑ፤ ከነፍስ ፈቃዳቸው የተጣረሱ የእነዚህ ኢንዱስትሪዎች መግለጫ ሲሆኑ በውስጣዊ ማንነታቸው ይረበሻሉ። ነገር ግን ብዙሃኑ እንደሆነው መሆን ነው የሚለውን የዲያቢሎስ አገዛዙን የሚያበልጽግ አስተሳሰብ ስላለ፤ ተያይዞ መጥፋት አማራጭ ተደርጎ ለብዙ ዘመናት ሐሰት በእውነት ቦታ ተሰይማ ስትመራ ስለቆየች፤ ከመከራ ጋር መኖር ፋንታችን ነው።

+++

ኢሉሚናቲ እና መሰል የመናፍስቱ ማኅበራት በተቀዳሚ ራእይና ተልዕኮ ሃይማኖትን ለይቶ ማጥቃት የሚል አጀንዳ ስላላቸው፤ በመዝናኛ ማዕከሎቻቸው በኩል የሚያሰራጩት መልዕክቶች የዲያቢሎስን ፍላጎት የሚያስፈጽሙ፣ የሥጋ ፍቃድን አግዝፈው የነፍስ ጩኸትን የሚያፍኑ፣ ሰማያዊ አኗኗርን ከሕይወት መስመር ላይ አሽሽተው በሚታይ ነገር ላይ ብቻ ጊዜን የሚያስመረኩዙ መልዕክቶች በመሆናቸው፤ እውነትም ታዲያ ትውልዳችን ከእምነት እሴቶች ተለይቶ በዝሙት መናፍስት ታስሮ ለየግል ለየግሉ የሚያለቅስ ቢሆን የሚያስገርም አይሆንም።

+++

ቡዳ የሚሆኑ መናፍስት ግዴታ ከሰው ላይ ብቻ ተነስተው አይመጡም። እንደነዚህ የርኩሰት መዝናኛ መንገዶችን ድልድይ በማድረግ በቀላሉ በማየት ብቻ ይዋረሳሉ። ለዚህ ነው ተዋናዮቹ ሲራቆቱ እዚህም ትውልዳችን የሚራቆተው። የሚያየውን ነገር ከውስጥ ያለው አጥፊ መንፈስ ወደ ውጪም እንዲገልጠው ዘመኑን፣ ሥልጣኔውንና የኢኮኖሚ አቅም አንጸባራቂነቱን እየነጠለ አስውቦ ስለሚያሳየው፤ ሰውየው ባየው ነገር ላይ ራሱን ለማግኘት ዕድል ብቻ የሚጠብቅ ይሆናል።
ይሄ የመናፍስቱ ውስጣዊ ጫና ሁለቱን ኢንዱስትሪዎች ተመጋጋቢ ያደረጋቸው በመሆኑ፤ የሩካቤ ትዕይንቶች የበዙበትን ፊልሞችና ሙዚቃዎች የተከተለው ወጣት፤ መድረሻው የወሲብ ፊልም ጥገኝነት ላይ ነው። ፊልሙ አሊያ ሙዚቃው ላይ በጨረፍታ የሚያሳዩት የዝሙት እንቅስቃሴዎች፤ ከውስጥ ላለው ዓይነጥላ የወሲብ ስሜትን በጫና ለመፍጠር ጥሩ ጉልበት ስለሚሆነው፤ በጨረፍታ አሊያም በከፊል ያየውን የሩካቤ እይታ በሙሉ አድማስ እንዲመለከተው ገፋፍቶ ገፋፍቶ የወሲብ ፊልሙን እንዲያይ የልበናውን ኃይል እያስጨነቀ ይመራዋል። እንኪያስ ብዙ የተበላሹ የመዝናኛ መልዕክቶችን ወደ ውስጥህ ባስገባህ ቁጥር፤ ከውጪ ቡዳ ሆነው የሚዋረሱትና ከውስጥ የእስራት አዚም ለመሆን የሚጠባበቁት መናፍስት፤ በምታየው ልክ መጥፊያውን አበጅተው የግል ዝሙት ቁራኛ አድርገው ያሰቃዩሃል።

+++

ስለዚህ ምን ይሻላል? ክርስቲያንም ሆነን አረማዊም ሆነን እንኖር ዘንድ እንደምን ይቻለናል? አሁን አንደኛው ፈተና የሆነብን ጉዳይ እኮ ዛሬ ዛሬ መንፈሳዊነትን ከአረማዊነት አግባብቶ ለመያዝ በሚደረገው ትግል ውስጥ ቢነግሩት የማይሰማ፣ ቢመክሩት የማይገሰጽ፣ ቢቀሰቅሱት የማይነቃ፣ ቢለምኑት የማይቀበል ሞገደኛ ጠባያትንና የውስጥ አመልን አበልጽገን ይዘን፤ በጎ ሲነገረን፣ ስናይ እና ሲደረግ አይስማማንም። ቢስማማንም አንሳተፍም። ራቅ ብለን እናያለን። ከሩቅ በመመልከታችን ክፍተት ውስጥ ታዛቢ ስንሆን፤ ለማፍረስ የሚቸኩል ስብዕና፣ ለመተቸት የሚሮጥ ቋንቋ፣ ለመጣል የሚሮጡ እግሮች፣ ለመገፍተር የሚፋጠኑ እጆች የመያዝ አዝማሚያዎችን እንደ ጋራ ጠባይ ስናስተናግድ ለምን ብለን አንጠይቅም። ታዲያ እንዴት ነው ነገሩ? ለምንድነው የምንደበላለቀው? ለምንድነው ረግቶ መቆየት የተሣነን?

ብዙ ቦታዎች ላይ መንፈሳዊ አቋማችን እየሄደ የሚቋረጥበት ምክንያት ይሄ ነው። መንፈሳዊነትን ከአረማዊነትን ጋር አንድ ላይ ተሸክመን ለማቆየት ስለምንጥር። መዝሙርንና ሙዚቃን ለማግባባት ስለምንጥር። የተቀደደ ጅንስንና ነጠላን ለማጣመር ስለምንሞክር። ፍቅረ ንዋይን ከፍቅረ መለኮት ጋር ለማቻቻል ስለምንዳክር። ውስጣዊ መረጋጋትን ለምቾት መቸኮል ጋር ደባልቀን ስለያዝን። ታዲያ እንዴት ይሁን? በአገራችን የሚነገር አባባል አለ። "ሁለት እግር አለኝ ተብሎ ሁለት ዛፍ አይወጣም" የሚል። እኛም ሁለት ገጽ አለን አንዱ መንፈሳዊ አንዱ አረማዊ ብለን እንኖር ዘንድ አንችልም።

ነጭ አርጎ የሰጠን ላይ ጥቁር እየለወሰንበት፣ በጎ ቃልን እንድንናገር የከፈተልንን አንደበት ነገርና ክፋትን ጨምረን አሰልጥነን ይዘን፣ ፍቅራችን ውስጥ ጥላቻ፣ እውቀታችን ውስጥ ምቀኝነት፣ ገንዘባችን ውስጥ ግፈኝነት፣ ምግሳችን ውስጥ አመፀኝነት፣ ችሎታችን ውስጥ ጨቋኝነት፣ ጸጋችን ውስጥ ተንኮለኝነት፣ ጥበባችን ውስጥ አጥፊነት #አቀላቅለን ይዘን ለሌላውም ስናቀርበው ይህንኑ የተደባለቀ ባቢሎንነትን ከትውልድ ትውልድ፣ ከዘመን ዘመን እያሸጋገርን አምጥተን የምንጓዝበት ጓዳና ሁሉ ወደ መከነው እያደረሰን፤ አንዱን ስንለው አንዱ፣ ተስተካከለም ስንለው እየተደመሰሰ፣ ጠራ ስንል እየደፈረሰ፣ አማረበት ሰንል እየጠወለገ ግልብጥብጡ የወጣ ዘመንና አኗኗር ላይ መቆማችንን ስንመለከት በእርግጥም ሳንጠራጠር 'መካን በዘመኑ ሁሉ የማይከናወንለት ሰው ብለህ ጻፍ' የሚለው የነብዩ ኤርሚያስ ትንቢት የኛ ገጽታ እንደሆነ እንገነዘባለን።
ስለዚህ ምን ይሻለናል? እንዴት ነው ነገሩ? ምን እንወስን?

## ✞ የወሲብ ፊልምና ከእምነት መሸሽ ✞

ወደ ሕይወታችን ውስጥ በተለያየ መንገድ የሚገቡ መረጃዎች፣ መርሆች እና አሳቦች ውስጣችን በመከማቸት የኑሮአችንን አቅጣጫና ሂደት የሚወስኑበት አጋጣሚ ሰፊ ነው። በዚህም መሠረት የምናየው እይታ፣ የምንሰማው ድምፅ፣ የምናስበው አሳብ፣ የምንውልበት ቦታ፣ የለመድነው ልማድ የሕይወታችንን ቀጣይ ጊዜ ዕድሉ ላይ የመወሰን ድርሻ ሲኖር፤ ወደ ውስጥ የሚገባው ጉዳይ ወደ ውጪም በተገለጠ ጊዜ ያንኑ የገባውን ነገር በሁኔታውና በጊዜው ክስተት ልክ የሚያንጸባርቅ ይሆናል።

+++

እንግዲያው፣ ወደ ውስጣችን ርኩሰት ሲገባ ወደ ውጪም የረከሰው ነገር ይገለጣል። ወደ ውስጣችን ክፋት ሲያድር ወደ ውጪም ያው ክፋት እየተገለጠ ይወጣል። ወደ ውስጣችን መርገም በዘለቀ ጊዜ ወደ ውጪኛው ክፍልም እርግማን የመቆየት ኃይሉ የጸና ይሆናል። ይህንን የሕይወት ጉዞ አሠራር ጠንቅቀው የሚያውቁት መናፍስት፤ የሚታገሉንም ቦታ እዚህኛው እውነት ላይ ይሆናል። ወደ ውስጣችን አመፃን ለማኖር፣ ርኩሰትን ለማንገስ፣ ጥፋትን ለማኖር፣ እኩይነትን ለመጀመር፣ ጋጠወጥነትን ለማሰልጠን፣ ቂምና ግፍን ለማስተማር በተለያየ መልኩና መስመር ከውጪ ወደ ውስጣችን ኃጢአትን ለማስገባት ይጥራሉ። ከነዚህ ከውጪ ወደ ውስጥ ከሚገቡት የመናፍስት መሣሪያዎች መካከል ዋና ዋናዎቹ ፊልሞች፣ ሙዚቃዎች፣ ጽሑፎችና ሥልጠናዎች ናቸው።

+++

የወሲብ ፊልሞችም ከመነሻው ሲመሠረቱ ተቀዳሚ ዓላማቸው ርኩሰትን ከፍ ለማድረግና የዝሙት ኃይልን በትውልድ አኗኗር መካከል ለማስፈን ሲሆን፤ በዚህም ተልዕኮዋቸው በጋሸበው ትውልድ አለማወቅና ለማወቅም አለመፈለግ ምክንያት በተገባ ተሳክቶላቸው ሲገኙ፤ ዘመኑ ወደ ማብቂያው መድረሻ ላይ የሚደርስበትን መግለጫዎች ገጽታው አድርጎ፤ የእምነት እውነታና ታሪክ እየተናቀ፣ እየተገፋ፣ እየተጨቆነ፣ አማራጭ እየተደረገ፣ በሌላ እየተተካ ስለቆየ፤ ዛሬ ላይ በቃ ከ"አቤቱ አድነኝ" ጸሎት ውጪም ሌላ ጩኸት ማሰማት መፍትሔ እስከማይሆንበት ድረስ ዓለምና ዜጓቿ በአንድነት የመጥፋት ዕጣ ውስጥ ውደቀን አስጨናቂ ጊዜ፣ አስጨናቂ ኑሮ፣ አስጨናቂ ዘመን ላይ ተገኝተን በብዙ የሕይወት መንገዶች ላይ ፈራ ተባ እያልን እንድንመላለስ ይኸውና ተገደን ቁጭ ብለናል። እግዚአብሔር ይማረን።

+++

በዝሙት መናፍስት የእስራት ኃይል ልብና ጊዜያችን የታሰረ ሲሆን፤ ወደ እምነት አምባዎች ለመጠጋት የምናደርገው የተሰካ ለመሆን እንዳይችል ገና ከመነሻው ላይ ፍላጎት በማጣት እና በመረበሽ ምክንያት ከባድ ይሆናል። የወሲብ ገጽታዎች፣ ቋንቋዎች፣ ድምፆችና ንባቦች ወደ ውስጣችን ገብተው፤ የመናፍስቱ አዚማዊ የሩካቤ ይዘት ያለው ቅርጽ ከሕሊናችን ላይ ስለሚታተሙ፤ ከውጪ ወደ ውስጥ የምናስተናግደው

የእምነት አካሄድና መንፈሳዊ ምግባራትን ለመሸሸ እንገደዳለን። በቃ ይሄ ግልጽ ጉዳይ ነው። የወሲብ ፊልሞችን አይተህ ስለጸሎት ስታስብ ራስን በመውቀስ የአጥፊዎቹ ስልት አማካኝነት ከሃይማኖት መሸሸ የሚጠበቀው ውጤት ነው። የወሲብ ጽሑፎችን አንብበህ ስለ ስግደት ስታስብ ራስን እንደ ኃጢአተኛ በመቁጠር የቁጭት ስሜት ምክንያት ከሰማያዊ የቅድስና ልምምድ መራቅ መፈለግ ሊከሰት የሚችል ግጴታ ነው።

ከመነሻው የከፉዎቹ ባለህቡዕ ማኅበራትም ፍላጎትና እቅድ ይኸው ነው። መዝናኛ በሚመስሉ የአእምሮና የነፍስ ማስከሪያዎችን በመጠቀም፤ ከእምነት ኃይል የመሸሸ ነገር  ከእያንዳንዱ ሰው ላይ በነፍስ ወከፍ ለቀማ ሸሸቱ የበለጸገ አቅም እንዲያገኝ አድርገው፤ ማሕበራዊ እሴትን መደምሰስ፣ የአባቶችን የሃይማኖት ታሪክና ቃልኪዳን ማዛነፍ ከዛ ማስካድ፣ የሕሊና ዝቅጠትን መጨመር፣ የሥነ ምግባር ክስረትን በማጽደቅ ዓለምአቀፋዊ አጀንዳዎቻችን ማስፈጸም ሌት ተቀን ለማሳካት የሚጥሩለት ጥልቅ ግባቸው ነው።

በዚህ ዘመን አጥፊው መንፈስ ግብረ-ገብነትን አጥፍቶ፤ የጾታ ነፃነትን ለዘመናዊው ትውልድ መብትህና ነፃነትህ ነው በማለት፤ በወሲብ ፍላጎት ትምህርት፤ የወንድ ለወንድ፣ የሴት ለሴት ጋብቻን መልክ እንዲኖረው በማገዝና በማበረታታት የስሜት ሥነ ልቦናን በሚያነቃቁና ጋጠወጥነትን በሚያደራጁ ሰዎች በመታገዝ፤ የክርስትናን የሥነ ምግባር ሥርዓት በማፋለስና በማርከስ ፈጣን የትውልድ ርኩሰትን አስፋፍቷል።

+++

የእምነትን መንገድ ለማሰናከልና የሰው ልጆችን ከሃይማኖት ለማራቅ ዲያቢሎስ ከሚጠቀምባቸው የስምሪት መንገዶች ውስጥ አንደኛውና ርኩሰቱን ከሚገለጥበት ግብሮች ውስጥ በዛሬ ዘመን ሰፊውን አድማስ የያዘው፤ የሰዎች ልጆች በአዳምና ሔዋን በኩል ከሕያው እግዚአብሔር የታደላቸው የሩካቤ-ሥጋን የተቀደሰ የአንድነት ትዳር የቡራኬ ሕይወት በመጠቀም ወደራሱ የግራ ዘመምነት መሣሪያ አድርጎ የመለወጥ የክፋት አሠራሩ ነው። ይህንን ተባርኮ የተሰጠውን የእግዚአብሔር ስጦታ ዲያቢሎስ በመለወጥ ወደ "ዝሙት አመፃ" ይቀይረዋል።

ከዲያቢሎስ አሠራር ውስጥ ዋነኛና መሠረታዊ አካሄዱ ነገሮችን #የመለወጥ ስልቱ ነው። ከቅድስና ወደ ርኩሰት፣ ከሰላም ወደ ብጥብጥ፣ ከፍቅር ወደ ጥላቻ፣ ከመተባበር ወደ መለያየት፣ ከመሰማማት ወደ መደናቆር። የዲያቢሎስ ዓላማ ይህ ነው። በመጀመሪያ ማጥመም፤ በሁለተኛው መለወጥ። ጌታችን መድሃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በሥጋ ተወልዶ ሲዛመደን፤ ጠላት ደሞ ከማኅፀን ጀምሮ በመቆራኘት አብሮ በመወለድ ዛር እየሆነ ከሚጠብቀን የበረከትና የቅድስና ሕይወት ለማስወጣት ይሞክራል። አባቶቻችን መቁጠሪያን ይዘው የቆዩበትን ዘመንና አኗኗር ለውጦ ጨሌ ያሲይዛል። ቀደምት ሌላውን ለማንሳት የሚፏፏጡበትን የታሪክ እውነታ ደምስሶ እርስ በእርሳችን የመተባተብ፣ የመገፋፋትና የመነቃቀል ታሪክ እንዲኖረን ይለውጠናል። በቁርባንና በስግደት ውስጥ የቆዩ አገልጋዮችን ለውጦ የአሉባልታ ወሬና ዘረኝነትን በተሞሉ፣ ቃሉ እንደዚህ ይላል ብለው በሚቀመጡ፣ የቤተክርስቲያንን ክብርና ልዕልና ከልባቸው ባራቁ አጋልጋዮች ይተካቸዋል። ዲያቢሎስ አንዴ ልብህና ቤትህ ውስጥ ከገባ በኃላ እንደቀደመው መኖር አይታሰብም። አሁን አንዳንዶቻችን ድሮ'ኮ አስቀዳሽ ነበርኩ አሁን ምን እንደነካኝ እንጃ ቤተክርስቲያንም ከሄድኩ ዓመት ሞላኝ እንላለን። በፊት ሰንበት እንኳን እሳለማለሁ አሁን በደጁም ማለፍ ትቻለሁ እንላለን። እምነቴ ላይ ጎበዝ ነበርኩ፣ ትምህርቴ ላይ ጎበዝ ነበርኩ፣ በሥራዬ ታታሪ ነበርኩ፣ ቤተሰቤ ጋር ፍቅር ነበረኝ ሰላም ነበረኝ፣ ትዳሬ ሰላምና ጸጋ የሞላው ነበረ፣ ገንዘቤ በረከት ያለውና የሚተርፍም ነበረ፣ ፈጣንና ተደማጭ ነበርኩ፣ ብዙ ደስታና ጓደኞች ነበሩኝ እንላለን። ዛሬ ምን እንደነካኝ በቃ እንደበፊቱ የሆነልኝ የለም። ጊዜው ሲሄድ እየተበላሸሁ መጣሁ። ሕይወት ከበደኝ እንላለን። የብዙዎቻችን አሳቦችና ድምፆች እንደዚህ ሆነዋል። ለምን? ዲያቢሎስ ወድቋላ። ዘሬ ብሎ ዛር ሆኖ ቁጭ ብሏል። አብሮ ተወልዶ አብሮ አድጓል። ወደ መጥፎው የመለወጥ ጉዞ ውስጥ የከፉ መናፍስት ወጥመድ የቱን ያህል በተወሳሰበና በተሰወረ መልኩ እንደተዘረጋ ብዙዎቻችን አንረዳም።

በዚህም የመለወጥ የጥፋት አሠራር ሂደት ላይም በመቆም፤ የወሲብ ፊልሞችን ኢንደስትሪዎች በመጠቀም፤ ከፉ መንፈስ የእምነት ምሪትና ሰማያዊ ጉዞ ከወየበበት ለሥጋ ስሜት ብቻ ከምንኖርበት ሕይወት ውስጥ ለመዝፈቅ መረቡን በሰፊው የኢንተርኔትና የመዝናኛው ምኅዋር ላይ ጥሎ ተጠማጆችን በየጊዜው እየጨመረ ይገኛል።

'አባዶን' ከተሰኘው የመልአከ መንክራት ግርማ ወንድሙ መጽሐፍ ላይ የተገኘውን የአንዲት እህታችን ተሞክሮ እንዲህ ይላል።

<u>አንድ ወቅት ላይ አንድ እህት እንዲህ አለች</u>

"...የቤተሰቤ ምኞት ትልቅ ነበር። ተምሬ ጥሩ ውጤት አምጥቼ እንዳኮራቸው ሁልጊዜ ይነግሩኝና ይመክሩኝ ነበር። እኔ ግን ምክራቸውን ጠብ እንደመፈለግ ቆጥሬ፤ እልኸ ያዘኝ። በዚህም የተነሣ አጥኚ ሲሉኝ፤ በር ዘግቼ እተኛ ነበር። 7ና ከ7 ዓመቴ ጀምሮ፤ የወሲብ ፊልም ተደብቄ ስለማዘውትር፤ ከትምህርቴ ይልቅ የበለጠውን ጊዜ የምጨርሰው ፊልሙን በመመልከት ነበር።

ይህ ፊልም ሱስ ከሆነብኝ በኋላ ግን፤ ከቤተሰብ ራቅሁ። እንደውም ትምህርት አልገባ አለኝ፤ ጭራሽም ፊደል እንኳ እየጠፋብኝ መጣ። በዚህም ማንበብና መጻፍ የማልችል መሃይም ሰው ሆንኩኝ። አእምሮዬ ተሰርቆ የማስበው ሁሉ፤ ያየሁትን ፊልም በመሆን፤ ፍላጎቴ ከአቅሜ በላይ ስለሆነ፤ ከቤተሰቤ ተለይቼ በመጥፋት፤ ሆቴል ቤት ተቀጥሬ አዲስ ሕይወት ጀመርኩ። በዚም ሥራዬ፤ ያየሁትን የፊልሙን ዓይነት ሰው ሆንኩ። ስለዚህ ወንዶቹም ሴቶቹም ሱስ ሆኑብኝ። በዚህም ምክንያት 9 ጊዜ ጽንስን አስወረድሁ።

ይህ አሁን አድጎ የሚታየው ልጄ 10ኛዬ ነው። እርሱም ቢሆን ለእኔ፤ ሌላ መከራ ነው የሆነብኝ። እንደባሌ ይቀጣኛል፤ እየደበደበ እጄን ሰብሮታል። አባቱን ስለማላውቀው በመከራ አሳደኩት። ከዘጠኙ መካከል አንድ እርሱ ቢተርፍ፤ እርሱም ደግሞ ዱላው ሰለቸኝ። ወይ አይማር፣ አይታዘዝ፣ አይሰማ፣ ሥራ አይወድ፣ በዱላ እያስፈራራ ገንዘብ ይቀማኛል። በዚህ ላይ ሱሰኛ ነው። የማያጨሰውና የማይጠጣው ነገር የለም። ሲሰክር የሚያደርገውን አያውቅም። 9ኙ ያስወረድኳቸው ልጆቼ ቢኖሩ ኖሮ፤ ቢያንስ ሦስት እንኳን ዕድለኛ ሆነው ያግዙኝ ነበር። አይ ዕድሌ! ምነው? ሞቼ ባረፍኩት"

+++

እንግዲህ የወሲብ ፊልሞች እስራትና የመናፍስት የአጥፊነት ወጥመድ ትሩፋታቸው እንዲህ አይነት ሰቆቃ ነው። በዲያቢሎሳዊ ፊልሞች ኢንደስትሪ ዓለማቀፋዊ ጫናም ውስጥ እምነትን ለማደብዘዝና ከሰው ልጆች የልቦና ፍቃድ ለመራቅ ከሄዱባቸው ስልቶች መካከል የፊልሞቹን ትዕይንቶች በጣም ዘግናኝ፣ የሰብአዊነት ክብር የሚረግጡ፣ አረማዊ ብሎም እንስሳዊ አካኋን የሚገለጥባቸው፣ የፈቃደኝነት እብደት የሚነበብባቸው፣ ከቤተሰብ አሊያ ከዘመድ አዝማድ ጭምር ጋርም ሩካቤ የመፈጸም ድርሰቶችን እየዘጋጁ ስለሚለቁ፤ አፍሪካውያን በዚህ አዚማዊ ሱስ በመጠለፍ ከሕይወታቸው እንዲሰናከሉ፣ የሥነምግባር ሞራልን እንዲጥሉ፣ ጤነኛ የተዳርና የቤተሰብ ኑሮ እንዳይመሠርቱ በቴክኖሎጂ ገመድ አርዝሞ በማሰር ብዙ ኪሣራዎች እንዲከሰቱ ሆኗል። ዘመናዊ የሚመስለው ትውልዳችን ከመቼውም ጊዜ በላይ የውስጥ ሕይወትም የውጪ ገጽታም በሽተኛና መከራ ቆጣሪ ሆኖ፤ በሠለጠነ ጊዜ መካከል የምዕራባውያንን በብልጭልጭ መናፍስታዊ ሽፋን የተለወሱ የቴክኖሎጂ፣ የርዮተ ዓለም የኢኮኖሚና የሳይንስ ጫናዎችን ለመቋቋም ሲል የቤተሰብንና የአከባቢን ትርምስምሶች አፍኖ ይዞ በግድ እየተማረ እየተማረ ከርሞ፤ እንጀራ ፍለጋ ለሥጋ ኑሮ ብቻ ሲዳክር ሲዳክር ቆይቶ፤ አሁን የረቀቀውን የአጥፊዎችን ጥቃት ለመረዳት እንኳን አጋጣሚውን እስኪያጣ ርቆ ጠፍቶ ሄደ።

+++

የማብቂያው ዘመን ላይ ለመገኘታችን ነባራዊ ምስክሩ፤ መናፍስታዊ አሻጥሮችን ለመገንዘብና ለመረዳት ምንም አይነት የውስጥ ፍቃዱ ስለሌለን፤ አዳምና ሔዋንን በእባብ ተሰውሮ ወደ ሞት ጎዳና የወሰዳቸው ጠላት፤ ዛሬም እኛም ጋር በቴክኖሎጂ አውታሮች፣ በየዕለት ኑሮ ክስተቶች፣ በማሕበረሰባዊ መዋቅሮች፣ ሕይወትን ለማቅናት በምናደርገው ትግሎች ውስጥ ተሰውሮ ወደ ዘላለም ሞት ጎዳና እየወሰደን ሲገኝ፤ ከመጤፍም ቆጥረን በዚህ ጉዳይ ላይ ትኩረት ልንሰጠው ስላልቻልን፤ በየቤቱ ሁሉም ሲሰቃይ፣ በየግሉ ሁሉም ሲንከራተት፣ እንደጋራም ምንም ነገር አልሳካ ሲለን እንመን ብንል አስቸጋሪ ነው።

+++

የምናሳልፈው ሁሉ የዓመፃ ጠባያትና የትውልድ መጋሸብ፤ ከፖሊቲካዊና ማሕበራዊ አውታሮች ጋር ብቻ የሚያያዙ ከመሰለን ተሞኝተናል። የሕዝባችን መተረማመስና በግራው መዝመም፤ በመንግሥታዊ መዋቅሮችና ተያያዥ ፖሊሲዎች የሚፈታ ከመሰለን ደንግዘናል ማለት ነው። ይኸው ስንት ዓመት አልነው አልነው አይደለም እንዴ?

ከ60ዎቹ ዘመን አንስተን ፖለቲካዊ ንድፈ አሳቦችን እየቀያየርንና የርዮተ ዓለም ትንተናዎችን እየሞከርን መጣን። አሁን ይሻላል ስንለው፤ ወደ የሚብሰው እየሄደ፣ አዋጣን ስንል፤ ኪሣራ እያመጣብን፤ አለፈልን ስንል፣ ጭራሽ እየቀረቀዝን ቁጭ አልን። በመሳካትና በመጣመም መካከል እንዲሁ እየዋተትን የፍልስፍናና የፖሊሲ ቤተሙከራ ሆነን ዘመናትን አቀራረጠን መጣን። ወደባሰው ሁኔታ በጣም በፍጥነት

የማንዘበላችን ምክንያቶች በብዙ ልሂቃኖቻችና ምሁራን አስተንትኖ ቢገለጽም ከዘላቂ መፍትሔ ግን የሚያስቀምጠንን የሰላምና የእፎይታ ጊዜያቶቻችንን ግን ማምጣት አልተቻለም።

ምክንያቱም የእግዚአብሔርን ረሳን በቃ። እምነት የኋላ ቀሮች ነው አልን። በባህልና በሃይማኖት መካከል ያለውን ድንበር አጠፋነውና ቀላቅለነው በልማድ ብቻ ክርስትናን ተቀብለን ቁጭ አልን። ዓለማዊና መንፈሳዊ አኗኗር ብለን በአንዱ የእግዚአብሔር መንግሥት ሥር እንኖር ዘንድ የሚያስፈልግበትን የሕይወታችንን መንገድ ወደ ሁለት ዓለማት አወቃቀር ከፍለነው፤ ለሥጋዊ ፍቃድና ፍላጎቶች ብቻ የሚሮጠውን ዓለማዊ፤ የሃይማኖትን ኃይልና የቃልኪዳን እውነት የሚይዘውን መንፈሳዊ፤ ብለን ሁለት አኗኗሮችንና አካሄዶችን ፈጥረን በዓለማዊነት ፍቺም ውስጥ ዓለማዊ ማለት ከሰማይና ከምድር ገዢ እግዚአብሔር ነገራት የራቀ ነው አልንና ተርጉመነው የዓመፃ ዘመናትን በሰጠነው የፍቺ ትንተና በኩል እየመነጨ ሲወጣ መልሶ ደሞ ግራ ይገባናል። ዓለማዊ ማለት ዓለም ውስጥ የሚኖር ማለት ብቻ ነበረ። ነገር ግን በተጣመመ ርኩስ መናፍስቶችን በሚያግዝ አተረጓገም ውስጥ መንፈሳዊነት በዓለማዊ ሕይወታችን ውስጥ ሊከሰት የሚያስፈልግበትን የነፍስ መስመር ዘግተነው፤ ዘመናትን አስቀድሞ ወደ ምድር የወደቀው ጠላት ወደ ዕድሜያችና ወደ ዕድላችን ገብቶ አጣመን የያዝነው ዓለማዊነታችንን ተጋርቶን ሲቆይ አሁን አሁን ላይ ይኸው ርኩሰትን፣ አመፃን፣ ግፍን፣ መሰደድን፣ መዘበራረቅን በብዛት ተለማምደን ስናበቃ ቅድስና የተራራ ያህል ሸክም ሆነብን። እግዚአብሔር ይማረን።

## ✞ የወሲብ ፊልም ለአስገድዶ መድፈር ያለው ተጽዕኖ ✞

በተደጋጋሚ እንደገለጽሁት የወሲብ ፊልም በተለይ በዚህ ክፍለ ዘመን ትውልድ ላይ ያሳረፉት ስውርም ሆነ ግልጽ መናፍስታዊ ጫና በሚገባ ባለመመርመሩና ባለመጠናቱ እንጂ፤ ያስከተሉት አይነተ ብዙ ቀላልና ውስብስብ ጥልቅ ችግሮች የተለያዩ መከራዎች እንዲከሰቱ መነሻ ምክንያቶች ሆነው፤ የትውልዱን ገሚስ የሕልውና፣ የስነልቦና፣ የሃይማኖት እና የሞራል ሥነ ምግባረ ሕይወት በእጅጉ ፈትነው አደጋም ላይ ጥለውት ሲገኙ፤ በጥገኝነት የቁራኛ አዚም ውስጥ ጠፍንገው በማሰር በስሜት ግፊት በኩል እያንደረደሩ ለሰፋፊ ማሕበረሰባዊ ውድመቶች እንዲሁም ዘግናኝ የወንጀል ድርጊቶች ውጤት እየሆኑ በገሐድ ቢስተዋሉም፤ አብዛኞቻችን ዛሬም ጥሬዎን በምትታየን የዓለም ውዥንብር ውስጥ ገና ሳንነቃ በሰመመን መካከል የተዋጠ እንቅልፍ ጭልጥ ብለን በቁም ተኝተን፣ ራሳችን፣ ቤተሰቦቻችን፣ ልጆቻችንና ወዳጆቻችንን ጨምሮ አንድ በአንድ በዲያቢሎሳዊ ወጥመድ ተይዘን ስንማቀቅ የቆየን በመሆናችን፤ የመናፍስት አገዛዝንና ፈተናን እንደ አንድ የኑሮ ክፍል በአኗኗራነት ለምደነው፤ የጋራ ፍዳችንም በመናፍስቱ አጥፊነትና መጠነ ሰፊ የጀርባ አጥቂነት በፍጥነት ተስፋፍቶ እንደ አገርም ብዙ ታሪካዊ ቁስለቶችን አሻራ እያደረገ ለሚመጣው ትውልድ እያስቀረ እንደሆነ ልናጤን ያስፈልገን ነበረ።

+++

ከወሲብ ፊልሞች የአፈዝ አደንግዝ ዲያቢሎሳዊ የዓላማ ግቦች መካከል በሚስጢር ማኅበራቱ እቅድ ተካተው እንዲጠፉ የተፈለጉት የሥነ ምግባር መሠረቶች፣ የሃይማኖት የጽድቅ ምግባሮችና የቅዱስ መንፈስ ፍሬዎች በዋናነት ሲሆኑ በተጓዳኝ ደሞ እንዲበራከቱ የተፈለጉት የዝሙተኝነት ገጽታዎች፣ የወንጀል ክንውኖች፣ የርኩሰትና የእርግማን ሥራዎች፣ ዛሬ ላይ የትውልዳችን የየዕለት ዜና 'ሪፖሮቶች' መሆናቸውን ስንመለከት፤ ሕይወታችን ከኋላው የአተላ ታሪክ እንዲይዝ ለዘመናት በህቡዕም በግልጽም ሲፋለም የቆየው ጠላት ዕድላችንን ብዙ ቦታ ላይ ሞክሮት ሲያጨነግፈው፣ በድሉም ደስ ተሰኝቶ፣ የራሱን ልጆችም ወልዶ፣ ለተጨማሪ ጥፋቶች አሁንም የሰውንና የዘመን አሰላለፍን ዋጅቶ፤ እየሠራ መሆኑንን ብዙዎቻችን በጣሞ ዘንግተናል። ችግር ካልደረሰብን፣ አደጋ ካልገጠመን፣ መከራ ካላየን የምንል ስለሆንን ተራ በተራ የችግርና የእፎይታ አልባ ስቃዮችን ገፈት ቀማሽ እስከምንሆን ድረስ መዘንጋታችን ይቀጥላል። እግዚአብሔር ይማረን።

+++

የወሲብ ፊልሞች ከመነሻው መጀመር፣ ማደግንና በከፍተኛ ፍጥነት በሁሉም የዓለም አገራት አቅጣጫ መንሰራፋትን ተከትሎ በአደገኛና ዘመናትን በቆየ የመናፍስቶች የተዋርሶ ግፊት ምክንያት በዓለማችን ብሎም በአገራችን እየጨመረና የርኩሰት አሠራሩም እየጋሸበ፤ ግፈኝነቱን፣ አሰቃቂነቱን፣ ጨካኝነቱንና ሕሊና ቢስነቱን እያሳደገ ከመጣው ተጠቃሽ የወንጀል ድርጊቶች ውስጥ አንደኛው ክፍል የአስገድዶ መድፈር ወንጀል ድርጊት ነው።

## ✞ የወሲብ ፊልም ለአስገድዶ መድፈር ያለው ተጽዕኖ ✞

ይሄን በርዕሱ የተገለጸውን አሳብ ለማስረዳት ምንም አይነት ሰፊ ትንተና አሊያ የማሳመኛ ቃላት አያስፈልገውም። ርኅራኄን በሕይወትህ ካስገባህ ሩኅሩኅ ትሆናለህ፤ የሰላምና የደስታ ቆይታዎችን ለማግኘት በጣርከው ልክ ሰላማዊና ደስተኛ ትሆናለህ፤ ለጨካኝነትና ለሰቆቃ ድርጊቶች የምትሰጠው ጊዜ ከበዛ ያው አረመኔ ሆነህ የሰው አውሬ ትሆናለህ፤ እንዲሁ የወሲብ ፊልሞችን በጊዜህም፣ በሕሊናህም፣ በምትሰጠው በታ መካከልም ወድደህ ካቆየኸው በተመሳሳይ የዝሙት ቀበኛ ሆነህ በወሲብ ጤናማ ያልሆነ ስሜቶች መሪነት እየተነዳህ የወንጀል ሰው ለመሆን ያለው ዕድልህ በእጅጉ ይገዝፋል።

" ዓይኖችህም ከሚያዩት የተነሣ ዕብድ ትሆናለህ።" የሚለው ቃል በኦሪት ዘዳግም 28፥34 ላይ የተገኘው ቃል ነው። እነሆ ዛሬም በወሲብ ፊልም ዲያቢሎሳዊ አደንዛዥነት የተነሣ ሕሊና እና ማስተዋል በመናፍስት የደባ ጉም ምክንያት ፈዝዘው የሰው ልጆች በአማዊ ስሜት ሲያብዱ ብዙ የአስገድዶ መድፈር ወንጀሎች የተፈጸሙባቸው ጊዜያት በተጨማሪ እንዲከሰቱና እንዲበራከቱ ግድ ሆኗል። እንግዲያው ታዲያ ምን እንጠብቃለን? የእግዚአብሔር መለኮታዊ ፍቅርና ኃይል በባሕሪያችን ውስጥ አልገኝ ሲል፤ ከኃጢአት የግፍ ሥራዎችና የአመፃ ክፉ ቀናት ለመጠበቅ የምናሳየው ፈቃድ ግልጽ ለመሆን አቅም ሲያጥረው፤ ለቡራኬና መንፈሳዊ የሃይማኖት እውነታዎች ልባችንንና ሕይወታችንን ለማስገዛት እምቢ ስንል፤ ፍላጎታችን የክፉ መንፈስ ፍቃድ ሆኖ ለጥፋት አድራሽነት መሣሪያ መሆናችን የሚጠበቅ ዕጣ ፋንታ ነው።

+++

ገና ሰይጣን አለ የለም እያለ የሚደናበር ትውልድ ውስጥ መናፍስት ጥልቅ የመደበቂያና ጥፋትን የማበልጸጊያ ሽፋን አግኝተው ብዙ አቅጣጫዎች ላይ እንደ አገርም ጭምር በነዚህ እንደ ዝሙት ፊልሞችና መሰል የአመፃ መዝናኛዎች በሚያመርቱት የርኩሰት አፍዝ አደንግዝ ማሰሪያዎች ምክንያት የሥልጣኔ ወቅት ያልነው ዘመናችን የሰይጣን ዘመን ሲሆን፤ አንዳንዶቻችን ገና የዕለት እንጀራ ውጣ ውረድ ላይ ነን። አንዳንዶቻችን ሳይንሱና ቴክኖሎጂውን ለመያዝ ሩጫ ላይ ነን። አንዳንዶቻችን የዓለምን ሁከት አንሰማም ብለን በራሳችን የድበታ ዓለም ውስጥ የምናዋዥቅ ነን። አንዳንዶቻችን ደግሞ ባጣነው ነገር ላይ ሙሉ የሆነ ነገር ለመፈለግ ስንደክም ስንደክም መንፈሳዊ ጥቅሞችና ጉዳቶች ተሰውረውብን በጥሬዋ ዓለም ብቻ ዝም ብለን እንመላለሳለን።

+++

በወሲብ ፊልም ሱስ የናወዘ ልቦና በዝሙት መናፍስት እስራት ውስጥ ውስጣዊ የማስተዋሉ ኃይሉ ስለሚደክም፤ ለቅጽበት የሕሊና ከሳሽነትን ረግጦ በመናፍስቱ ግፊት በመነዳት የማመዛዘኛ ቀልቡን ስለሚያጣው የአስገድዶ መድፈር ተሳታፊ ወንጀለኛ ለመሆን አስቀድሞ ጭንቅላቱና የአኗኗር ስልቱ በቀላሉ በር የከፈተ ነው። ስለሆነም ግለሰቡ ቁጭ ብሎ በሚያያቸው የምናብ ሰይጣናዊ ስዕሎች መንፈሱ የነፍሱን መንፈሳዊ ክፍል ስለሚያፍነው፤ ያንን ሲያየው የቆየውን በሕሊና የተሳለ የዝሙት ጠባይና ተነሳሽነት በክፉ ቀን በክፉ መናፍስት በኩል ወደውጪ ይገልጠዋል። አንድ ቀላል ምሳሌ ስናነሳ፣ በአንድ ሸራ ላይ ተጸንባርቆ የሚታይ ምስል(projected image) ቢኖር፤ ሸራው እንዲያሳይ የሚገደደው ያንኑ ምስል ብቻ ነው። በዚሁ አይነት አሠራር የዝሙት መናፍስትም ውስጣዊ ሕይወትን የመቆጣጠር ተጋቦታቸው ፈጣን በመሆኑ ግለሰቡ እንደ ሱስ በየጊዜው ሲያየው የቆየውን ምስል በሕሊናው ሸራ ላይ በምናባዊ መልኩ ስለሚያንጸባርቁት፤ ሰውየው በምንም አይነት ሥጋዊ ጥበብና ዘዴ ከዚህ የውስጥ ፈተና ለማምለጥ እንዳይችል የጥፋት መንፈሶቹ የእምነት ሂደቶቹን ጥንካሬ ይሸረሽሩትና ገፍተው የሚፈልጉት ነጥብ ላይ ሲደርስ ይተዉታል። ስለዚህ ነው እጅግ የበዙ ሰዎች በሥነልቦናዊ ዘዴ ማለትም ለምሳሌ በማረሳሳት፣ ጊዜን በመጽሐፍትና ከሰዎች ጋር በመሆን በማሳለፍ፣ ስፖርታዊ እንቅስቃሴን በማድረግ መነቃቃትን ለመፍጠር ጥረት አድርገው ምናልባት የተወሰነ ጊዜ ከሩካቤ ፊልሞች ሱስኝነት ቢላቀቁም መልሰው ግን የሚወድቁት። የክፉ መናፍስት አሠራርና የጥፋት አገዛዝ የሚመከተው በመንፈሳዊ ጥበብና በመንፈስ ቅዱስ ስምና ኃይል እንጂ በሥጋዊ መፍትሔዎች በፍጹም አይደለም።

+++

ከነባራዊ ክስተቶችና እውነታዎች ላይ በመነሣት በእርግጠኝነት አስርጾ መናገር የሚቻለው(ሰሚ ካለ) የወሲብ ፊልም ኢንዱስትሪዎችና አቀርቦቶች በእጅጉ ጨምሮ በዓለም አገራት ውስጥ መስፋፋት በጀመረበት ልክ እንዲሁ ጎን ለጎን የአስገድዶ ደፈራ ወንጀሎችና ጾታዊ ትንኮሳዎች በተመሳሳይ ጨምረዋል። በተለይም ከተማ ቀመስ በሆኑ የቴክኖሎጂ ምርቶች በተሰራጨባቸው ቦታዎች ላይ ይህ

የበደል ፍሬ በተገለጠ መልኩ ተስተውሎ ለማንኛውም ለማጤን ፈቃደኛ ለሆነ ሰው ሁሉ የርኩሰቱ ገጽ ይታያል።

+++

መንግሥታት ስለዚህ የወሲብ ኢንደስትሪ እጅ ጠምዛዥ ትውልድ አጨንጋፊነት አያውቁም ብላችሁ ምስኪን እንዳትሆኑ። የሲጋራና ትምባሆ ውጤቶች ሲመረቱ ማሸጊያቸው ላይ "ጤናን የሚጎዳ" የሚል ማስፈራሪያ በመንግሥታቱ ደንብ መሠረት እንዲጽፉ ለአምራቾቹ ከመደነገግ ባለፈ ምርቱን ለመቆጣጠር የሚችሉበትን ሥልጣን በተገባ መሬት አውርደው ምርቶቹን አለመከልከላቸው << ሰው የፈለገውን የመከተል መብት አለው >> ከሚለው የሚስጢር ማኅበራቱ ዲሞክራሲ መሰል የአስገዳጅነት የጀርባ ተጽዕኖ ውስጥ መንግሥታቱ የተጨፈለቁ ስለመሆናቸው ማረጋገጫ ነው።

+++

በአብዛኛው ጊዜ ከብዙ የግፍ ወንጀሎችና የአመፃ ሁከቶች በስተጀርባ የርኩሳን መናፍስት በመሪነት የታገዘ የሕሊና ተምዦኝነት የድርጊቶቹ መነሻ ሲሆን፤ በውስጣዊውም ሆነ በውጫዊያዊ ኃይል አሳብ አመንጪነት፣ አቀናጅነትና አስፈጻሚነት በኩል የሚከናወኑ በሚሆኑበት ጊዜ፤ በመናፍስቱ ወጥመድ ሥር የገባው ግለሰብ በወንጀል ድርጊቱ የተግባር ሂደት መነሻና መድረሻ ጊዜ መካከል በግማሽ ልቦናው ሰው፣ በግማሽ ልቦናው ደግሞ ርኩስ መንፈስ፣ የሚሆን ሲሆን፤ አንዳንዴም መንፈሱ በሙሉ ኃይሉ ልቡን ስለሚይዘው ራሱን ሳያውቅ ወንጀሉን እንዲፈጽም ያደርገዋል። በዚህም ምክንያት ብዙ ወንጀል ፈጻሚ ግለሰቦች፤ በደም የተነከረ ስለታማ መሳሪያዎችን ከያዙ በኋላ፣ ሰው ከከፍታ ላይ ወርውረው ከጣሉ በኋላ፣ በዱላ አሊያም በብረታማ ነገሮች ቀጥቅጠው ከገደሉ በኋላ፣ በጦር መሳሪያ ተኩሰው ካቆሰሉ ወይ ሕይወት ካሳለፉ በኋላ፣ እሳትና ተቀጣጣይ ፈንጂዎችን አስነስተው ንብረት ካወደሙ በኋላ፤ መንፈሱ ከልቦናቸው ባወቀ ለቀቅ ስለሚል ከሕሊናቸው ማገናዘብ ጋር የተመለሱት ግለሰቦች በጥልቅ ድንጋጤ፣ በከፍተኛ ፍርሃት፣ በማያባራ መርበትበት ውስጥ የሚገኙ ሲሆን፤ ከሕሊናና ሕግ ፍርድ አስከትሎ በዘወትር ጸጸት ሥር ስለሚወድቁ ከራሳቸው ጋር በመጣላት ነፍሳቸውን ሊያጠፉ ይችላሉ። እንዲሁ አስገድዶ የመድፈር ወንጀሎችም በተመሳሳይ በመናፍስቱ ግፊትና የልብ መሰወር በኩል የሚፈጸሙ የዲያቢሎስ የከሳሽነት ውጤቶች ናቸው።

+++

የአስገድዶ መድፈር አስገዳጅ ስሜቶችን ለመፍጠር የወሲብ ኢንደስትሪዎች የሚያመርቱት ፊልምና ምስሎች መነሻ ምክንያቶች የሚሆኑበት አጋጣሚ እጅግ ሰፊና የበዛ ነው። በዝሙት ቁራኛነት የተለከፉ ሰዎች ከቁጥጥራቸው በራቀ የግንፍልተኛ ስሜት መሪነት ተገድደው ፊልሞቹን ለማየት በመናፍስቶቹ የሚገደዱትን ያህል፤ በተመሳሳይ ለአስገድዶ መድፈር ድርጊት የሚጋበዙ ወገኖችም ለተያዙበት መንፈስ መሣሪያ ሆነው በጠላት ፍቃድ ሥር የሥጋ ፍላጎትን ለማሟላት በሚሰጡት ትንሽ ክፍተት ውስጥ ብዙ ስህተት ይሠራሉ።

+++

ከዚህ አልፎ ተርፎ የዝሙት ፊልም ኢንደስትሪዎቹ በራሳቸው የፊልም ድርሰትና ዝግጅት ውስጥ የአስገድዶ መድፈር ትዕይንቶችን እንደመዝናኛ ክፍል አድርገው በማቅረብ፤ የሰዎች አእምሮ ነውርን እንዲለምደው፣ ወንጀልን እንደ እርካታ እንዲቆጥረው፣ ጥፋትን እንዲንቀው የሚያሰለጥኑ በጣም አደገኛና አጥፊ የዘመናችን ትውልድ መርዞች ናቸው። በተጨማሪም የዲያቢሎስ ጉዳይ አስፈጻሚዎቹ በሚሠሩት ፊልሞች ላይ በተዋናይነት ገጸ ባሕሪይ ይጫወቱት እንጂ፤ በፊልማቸው ይዘት ላይ ግን የአስገድዶ መድፈሩን አረማዊ ርቀት እጅግ ሰይጣናዊ ከፍታ ላይ ለማድረስ ከሄዱበት አሠራሮች መካከል የደም ትስስር ያላቸው ቤተሰቦችና ዘመዶች የወንጀል ክንውኖችን በነጻነት እየፈጸሙ የሚያሳዩ ድርሰቶችን በማዘጋጀት አባት ልጁን በመድፈር ሲቀጣ፣ እናት በልጇ ስትደፈር፣ እህት በወንድሞቿ ጥቃት ሲደርስባት እያሉ በማቅረብ፤ እንስሳዊ ስሜትን በዘመናዊው ትውልድ ላይ ፈጥረው፤ የሰው ልጅ የማገናዘቢያ አቅሉን ስቶ ለመናፍስቶች የግብር ጭዳ ሆኖ እንዲኖር ያደረጉትም ጥረት ብዙ ቦታ ላይ ተሳክቶ ይኸው ዛሬ እንኳን በውጪው ዓለም ቀርቶ እዚሁ እኛም አገር ሕፃናት ሲደፈሩ፣ ልጆች በገዛ የቤተሰብ አባላት ሲጠቁ፣ ወንድ ልጆችም ሳይቀር አረማኔያዊ ተግባር ሲፈጸምባቸው እየሰማን ነው።

ስለዚህ ምንድነው የምንጠብቀው ጎበዝ? ምን እስኪመጣ ነው እንዲሁ ዝም ብለን የምንቀመጠው? ለምንድነው የማታስተውሉት? እንደ ጋራ ዳፍንት ሆኖብን ዝም ብለን በአዙሪት ኑሮ እንድንኖር ያስገደደን የዲያቢሎስ ሠራዊት ላይ መቼ ነው የምንነቃው? "አባት ልጁን ደፈረ" ከሚል ሰይጣናዊ ዜና የተሻለ

ኑሮአችን በመናፍስት የተከበበ ስለመሆኑ ምን አይነት ማረጋገጫ ነው የምንፈልገው? "ሕፃናት ወንዶች በወንዶች ተደፈሩ" ከሚል ኢትዮጰያዊ (ኢትዮጵያዊ እኮ ነው ወገን) ድምፅ የበረታ የረከሰ የአጋንንት ዘመን ላይ ስለመገኘታችን የሚያረጋግጥ ምን አይነት ቃል ቢመጣ ነው የምንበረግገው? እውነት ምን ቢመጣ ነው ማሕበረሰቡ ውስጥ ማሕበረሰብ ሆኖ ያለን የጥፋት ሠራዊት ለይተን የምናውቀው? ለምንድነው እንደዚህ አይነት የአራዊታን ሰቅጣጭ ዜናዎች ከልብ ውስጣችን ቆይተው የማይጠዘጥዙን? ለምንድነው እንደነዚህ አይነት ዘግናኝ ድምፆች እስከ አጥንታችን ቅዝቃዜ ድረስ የማያሳምሙን? ለምንድነው የተቀደሰች አገር ላይ እንኖራለን የምንል ሕዝቦች ውስጥ እንደዚህ አይነት መርዶ ሲወጣ ያላፈርነው? ለምንድነው የሌላው ችግር አልታይ ብሎን እንደ ሕብረተሰብ አንድ ጊዜ በጅምላ የፈዘዝነው? ከማሕበራዊ ድረገጾች የወረት ቀናት ውጪ እነዚህ የዲያቢሎስ ውጤቶች ሰርገው ለብዙ የእውነት ቀናት ያላስጨነቁን ለምንድነው? ካስጨነቁንስ ለምንድነው ወዲያው ከሕይወታችን በቶሎ የሚርቁት? እስኪ ለምንድነው? ለነገሩ በማብቂያው ዘመን ለክፉው ዕድል የተገኘ ትውልድ በየግል በየግል ቤቱ ችግር እየመጣ ከአቅሙ በላይ ካላሰቃየው ቶሎ አይገባውም። እነሆ ተጨማሪ የሰቆቃ፣ የምሬት፣ የጭካኔ ዜናዎችን እያስተናገድን በየመንደራችን መጮህ ስንጀምር ገና ያኔ ለመንቃት እንጀምራለን።

## ✞ ከወሲብ ፊልም ጥገኝነት እንዴት እንላቀቅ? ✞

በወሲብ ፊልም የሱሰኝነት እስራት ውስጥ መውደቅ መንፈሳዊ  እስራት ነው። በሚታይ ሰንሰለት፣ በሚዳሰስ እጀ ሙቅ፣ በሚንቀሳቀስ ብረት የሚከናወን እስራት አይደለም። የክፉ መናፍስት አዚማዊ እስራት ነው። ይሄን በተገባ አስርጾን ከመገንዘብ ስንጀምር የመፍትሔ አቅጣጫውንም ከመነሻው ለመረዳት መንገድ እናገኛለን።

ብዙ በዚህ ዲያቢሎሳዊ ፈተና ውስጥ የወደቁ ወገኖች ታዲያ የማይገነዘቡት ጉዳይ ይህንኑ ነው። የወሲብ ፊልም ቀበኝነት ከአጥፊ መናፍስት ጋር ሳይሆን፤ ከፈቃደኝነት የሥጋ ፍላጎት ላይ የተነሣ የሥጋ ሱስ ጋር ብቻ እያይዘውት፤ ከመፍትሔውም ለመላቀቅ የሚሄዱባቸውም መንገዶች በአብዛኛው የሚከተሉት የሥጋ መፍትሔዎች ናቸው።

☞ ስነልቦናን የማረሳሳት ዘዴን ለመጠቀም ጊዜን በተለያዩ ተጨማሪ ሥራዎች፣ ስፖርታዊ

እንቅስቃሴዎችና መዝናኛዎች ማጣበብ

☞ መጽሐፍትን፣ ሙዚቃዎችንና ሌሎች ጊዜ ማሳለፊያ ነገሮች ላይ ትኩረት በመስጠት አእምሮን ፋታ

ለማሳጣት መሞከር

☞ ከጓደኞች፣ ከቤተሰቦችና የቅርብ ሰዎች ጋር በመሆን የብቸኝነት ጊዜ እንዳይመጣና የሱሱ ጥያቄ ተያይዞ

እንዳይከሰት ቀድሞ መንገድ መዝጋት

☞ ባስ ያለ ደረጃ ላይም ደርሶ የሱሱ እርከን ወደ ጭንቀት መለወጥ ሲጀምር የሥነልቦና ባለሙያ ማማከር

እንግዲህ እነዚህንና ሌሎች ያልተጠቀሱ ሥጋዊ መፍትሔዎችን በመከተል ብዙ ሰዎች ከሩካቤ ፊልሞች ሱሰኝነት ለመላቀቅ ይጥራሉ። በእርግጥ ለተወሰኑ ሳምንታት ወይንም ቆይታዎች ከአዚማዊ የውስጥ ጥያቄው ሸሸት ቢሉም፤ ዘላቂና እስከወዲያኛው የሚገላግሉ መፍትሔዎች ግን አይደሉም። በዚህ ምክንያት በሌላ ጊዜ ላይ ደግሞ ችግረኞቹ መልሰው በፊልሞቹ ሱሰኝነት ሲቸገሩ፤ ከጥገኝነቱ መላቀቅ እንደማይችሉ ስለሚሰማቸው የበለጠ ተስፋ መቁረጥና ጭንቀት የሚጀምርበት አጋጣሚ ሰፊ ነው።

#አስተውሉ! መንፈሳዊ ጥቃቶች በመንፈሳዊ ክንድና አቅም በኩል ነው የሚመከቱት። በክፉ መናፍስት ጥበብና አሠራር የመጣ አበሳ፤ በመንፈስ ቅዱስ ኃይልና ጥበብ ብቻ ነው የሚመለሰው። በአጥፊ ጠላቶች ቀጥተኛም ይሁን ተዘዋዋሪ ምክንያት የተፈጠረ ማንኛውም አይነት ችግር፤ በሰማያዊ የአምልኮት ልምምድና ብርታት በኩል ነው የሚቀረፈው። ከዚህ ውጪ ያሉት ሥጋዊ ጥበቦችና አካሄዶች ተጨማሪ የመፍትሔ መንገዶች እንጂ በምንም መልኩ ቀዳሚ የችግር መፍቻ ቁልፍ ሆነው የዲያቢሎስን ኃይል አይቋቋሙም።

<u>ስለዚህ ምን እናድርግ</u> ?

### ❶· <u>የአምልኮት ስግደት</u>

እነዚህ በዓለም አቀፍ የሴራ ደባና የጥፋት መናፍስቶች በኩል እየተመረቱ የሚወጡት የዝሙት ፊልሞችና ተያያዥ ምርቶች ሁሉ ከሕይወታችን ውስጥ አዚም ሆነው ገብተው በጥገኝነት ቁራኛ አስረውን ከሆነ፤ እስራቱን የመበጠሻ አንዱ መጋዝ የዘወትር የአምልኮት ስግደት ነው።

ከስሙ እንደምንረዳው የአምልኮት ስግደት የማምለኪያ ቅጽ ማስገቢያ ስግደት ነው። የአምልኮት ስግደት ከነፍስ ውስጥ በየጊዜው ያድግ ዘንድ የሚገባውን የመለኮት ኃይል እየጨመረ የሚመጣ ስግደት ነው። ይሄ የሚገባው በመስገድ የሚጠቀምበት ሰው ብቻ ነው። እነሆ ታዲያ ከእውነት የፍቅር መሠረት ካለው የእምነት መነሻ ላይ አስጀምራችሁ መስገድ በመናፍስቱ በኩል ተጠፍንጎ የተጠመጠመውን ሰንሰለት የሚገዘግዝ መቁረጫ ነው። እንግዲህ ልብ በሉ። እየተገዘገዘ የሚቆረጥ ሰንሰለት ሙሉ በሙሉ እስራቱን ለመበጠስ ሁለት ነገር ይፈልጋል። አንደኛው እየገዘገዙ መቆየት፣ በሁለተኛው የግዝገዛውን ጉልበት እየጨመሩ መሄድ ያስፈልጋል። አሁን ወዲያው መስገድ እንደጀመራችሁ ወዲያውኑ ትልቅ ለውጥ ማየት የምትፈልጉ አላችሁ። እንደዚህ አይሆንም። አስታውሱ። ክፉ መንፈሱም እስራቱን እያጠበቀ እያጠበቀ ነው የሚመጣው። በአንዴ ግጥም አድርጎ አያስርም። የመታሰር ሂደት ቁልቁል የመውረድ ገጽታ ምሳሌ ስለሆነ መቼ ተንሸራተን ታች ሸለቆ ጋር መቼ እንደደረስን ባለማስተዋል ስለምናሳልፍ እንጂ፤ አጥፊዎቻችም የጊዜ ሑደትን ጠብቀው ነው የሚሠሩት። ስለዚህ ቀስ በቀስ የታሰረ ገመድ፤ ቀስ በቀስ ነው የሚፈታው። ችግርን የመቅረፊያ መንገድ ገና ሲጀመር በዕውቀት ይታገዛል። መንገዱ ላይ ደሞ የጊዜ እገዛን ይፈልጋል። የመፍቻ አቅጣጫውን አንዴ ከተገነዘብን በኋላ የመፍታቱን ሂደት ሳያቋርጡ በተገኘው አቅጣጫ በኩል በመዞር ከጊዜ ጋር ጨርሰን የምንፈታው ጉዳይ ይሆናል። የወሲብ ፊልሞች እስራት መፍቻ መነሻ መፍትሔው አንዱ የአምልኮት ስግደት እንደሆነ አወቃችሁ። ስለዚህ ቀጣዩ ከጊዜ ጋር ሳያቋርጡ በየዕለቱ እየጨመሩ በመስገድ መበርታት አንድ በአንድ የአዚሙን የቋጠሮ ክሮች እየበጠሰ የሚሄድ ይሆናል።

## ❷· ጸሎት

ጸሎት የሰማዩን አባት የምናነጋግርበት ቋንቋ ነው። እዚህ ጋር በጣም ትልቁ ችግራችን ሰውን መፍትሔ ፍለጋ የምናማክረው ያህል እግዚአብሔርን በጸሎት አናማክረውም። ምክንያቱም የእግዚአብሔር መንፈስ ከሥጋ የተሰወረ ረቂቅ ስለሆነ የሚሰማንና መልስ የሚሰጠን አይመስለንም። ብዙዎቻችን በጣም ቸኩሎች ነን። ከእግዚአብሔር ይልቅ ሰውን የምናማክርበት ሌላኛው አመንክዮም ይሄው ችኩልነታችን ነው። ሰው ወዲያውኑ በሰውኛ ቋንቋ መፍትሔ ነው የሚለውን ድምፅ ስለሚያሰማን፤ ስንሮጥ የምንገኘው ሰው ፍለጋ ነው። በአጽንዖት ግን ያዙ። የትኛውም የምድር ሰው በአብዛኛው የሚያማክራችሁ ከእውቀቱ፣ ከልምዱና ካለበት የጊዜና የሁኔታ አንጻር ነው። የሚነግራችሁ መፍትሔ ፍጹም ትክክል እንኳን ቢሆን፤ እያንዳንዱ ውስጣዊ ስሜታችሁን እንደናንተ ሆኖ ማንም አይገነዘብላችሁም። ይሄ ተፈጥሮአዊ ግዴታ ነው። ስለዚህ አትሞኙ። በየቀኑ አስቀድማችሁ ለሰማዩ አምላክ በጸሎት አማክሩ። ግጥም አድርጋችሁ አምናችሁ አማክሩ። አይምሰላችሁ በእውነት። በጣም የሚሰማ ገር አባት ነው። መለኮታዊ መዳፎቹ እርዳኝ እያሉ የሚጮኹ እጆችን ለመያዝ ለአንዲት ሰከንድ ታጥፈው አያውቁም። ስለዚህ በዚህ የመናፍስት ወጥመድ ውስጥ ገብታችሁ የምትሰቃዩ ወገኖች፤ ዘወትር ከወጥመድ አውጣኝ እያላችሁ ጸሎት ቤት በገባችሁ ልክ አሳስቡ። መቼ መቼ አሳስቡ? ዘወትር። እዚህም ጋር ጥልቅ የሆነ የመንፈስ ቅዱስ ሃይማኖታዊ አሠራርን ስለማንገነዘብ "በቃ እግዚአብሔር ሁሉን አዋቂ ነውና አንዴ ከነገርነው ይበቃል" ብለን የተሳሳተ ግንዛቤ እንይዛለን። በእርግጥ ለእግዚአብሔር አንዴ መንገር አይደለም ሳንነግረውም ችግራችንን ለማስተካከል የዋህ ልቡናው ሁሌ ወደኛ ነው። የነገሩ መጠላለፍ ግን ያለው እኛ ውስጥ ካለው ርኩስ ጠላት አንጻር ነው። መንፈስ ጸሎት ባደረግን ቁጥር በመጀመሪያ ለማስቆም ይታገል ይታገልና፤ ስንጸናበት እርሱ እየደከመ እየደከመ ይመጣል። ስለሆነ ውስጣችን አዚም ሆኖ ያለው ጠላት አጠብቆ የእስራት ሰንሰለቱን የያዘበት ክንዱን ለማዛል ጸሎቱ በየቀኑ በእውነተኛ የአቅም ልክ ድረስ ነው መደረግ ያለበት። በጣም የሚያሳዝነው ግን ብዙዎቻችን፣ በመናፍስት የተጨነቅነውን ያህል መናፍስቱን በየዕለት ጸሎት ለማስጨነቅ ጠንካራ የውስጥ ሞራልና ፍላጎት የለንም። ፍላጎቱ ግማሽ የሆነበት ወይንም ትንሽም ብትሆን ክፍተት ያለበት ሰው ደሞ ላለማከናወን፤ በፍላጎቱ ክፍተት ልክ ሰበብ ይፈልጋል። ስለዚሁ ችግሩን እየዘከረ የሚቀመጥ ሰው ይሆናል ማለት ነው። ግን አስታውሱ #ፍጹም_የታመነ_ቃሉ እንዲህ ይላል፡ " <u>አምናችሁም በጸሎት የምትለምኑትን ሁሉ ትቀበላላችሁ</u>።"
(ማቴ. 20፡21)

## ❸· መቁጠሪያ

ሌላው በሩካቤ ፊልም ሱሰኝነት ውስጥ ጠፍንገው የከረቸሙንን ጠላቶች የምናደክመው በመቁጠሪያ ነው። እዚህ ጋር መሠረታዊ መረጃ የምሰጣችሁ፤ በመቁጠሪያ መናፍስትን በምትቃወሙበት ሰዓት ላይ ርዕስ እየሰጣችሁ አቃጥሏቸው። ምን ማለት ነው፣ ለምሳሌ አሁን የዚህ ክፍል ትምህርታችን 'እንዴት ከወሲብ ፊልም ሱሰኝነት እንላቀቅ' የሚል ነው። የዝርዝር ጉዳዩ መምሪያ አድራሻ በርዕሱ ውስጥ የተጠቀለለ ነው። እንዲሁ መናፍስቱንም ስትቀጠቅጡ የችግራችሁን ዝርዝር ጠቅልሎ የሚይዝ ርዕስን በመስጠት ማድከም ያስፈልጋል። "በዚህ ጥገኝነት ውስጥ ያሰራችሁኝ ጠላቶች" ብለን ለብቻ ጠርተን ነው መቀጥቀጥ ያለብን። ለምንድን ነው ይሄ፣ አንደኛ ያንን የእስራት ሥራ እየከወነብን ያለው መንፈስ በቀጥታ ባለጉዳይ አድርገን

እንድንቀውረው የመንፈስ ቅዱስ ኃይልን እናነጣጥርበታለን። ሁለተኛ፣ መንፈሱን እንደነቃንበት ማገናዘቢያ ስለሆነ፤ የተሰወረው ጠላት ግልጽ መምጣት ይጀምራል። ይሄ ደግሞ የፍልሚያውን ጉልበት እንድናሳድግ አቅምና ብርታት ይሰጠናል። ሦስተኛ መናፍስት ግብራቸው ስለሚለያይ፤ ዝም ብለን በደፈናው ከምንቀጠቀጥ የባሰ ችግር እያመጣብን ያለውን መንፈስ ቅድሚያ ለማስቆምና እርሱም ያንን ችግር እያከናወኑ ባልሆኑ መናፍስት ተደብቆ፤ ደካማ መናፍስትን እያጋለጠ ግብሩን ቀጥሎ የአምልኮታችንን ሞራል "እየቀጠቀጥኩም ሥራውን አያቆምም እንዴ?" ብለን የምንጎዳበተ አሳብን አበልጽጎ እንዳያጠቃን እየለየን ነው ማድከም ያለብን። ስለዚህ ሁሌ መቁጠሪያውን ሰትጠቀሙ የየዕለቱ አልከናወን ያሉ ችግሮችን እያያችሁ "ይሄን ይሄን የምታደርግ መንፈስ አንተ ለብቻህ ታስረሃል" ብላችሁ ቀጥቅጡት። ትልቁ ነባራዊ እከል እየፈጸመ ያለውን ጠላት በእንዲህ መልኩ ለብቻው ከቀጠቀጣችሁ በኋላ ደግሞ "አጠቃላይ በሕይወቴ ውስጥ ያደፈጣችሁ ታስራችኋል!" ብላችሁ ደግሞ ከሌሎቹ ጠላቶች ጋር አንድ ላይ ማድከም ብዙ ሥራውን በጊዜ ሂደት እንድታከሽፉት ያደርግላችኋል። አይመስላችሁ በርቱ።
" <u>በእግዚአብሔር የምታምኑ ሁላችሁ፥ በርቱ ልባችሁም ይጥና</u>።"
(መዝሙረ ዳዊት 31፥24)

## <u>❹· ፊልሞቹን አለማየት</u>

ይሄን ገና ርዕሱን ስታዩ ልትደናገሩ ትችላላችሁ። ከጅምሩ ላለማየት አይደለም ወይ መፍትሔ የምንፈልገው እንዴት ነው አትዩ የሚለው ጉዳይ ጥያቄ ይሆናል።
አንድ ግን በጣም ግልጽ መሆን ያለበት ጉዳይ አለ። አንድ ወቀት ላይ ቅዱስ ጌታ ለደቀመዛሙርቱ የእምነትን ኃይልን ባስረዳቸው ጊዜ "የሰናፍጭ ቅንጣት ያህል እምነት ቢኖራችሁ የሚሳናችሁ የለም" ብሎ ነበረ። ርኩስ መንፈስ ሁሌ ታዲያ አምላክን በተቃራኒው አቀጣጫ አበክሮ የሚከተለው ፍጡር ነውና በእርሱ የአሠራር ስልት በኩል ደግሞ ይሄን ያስፈጽማል። "የሰናፍጭ ያህል ስህተት ስትሠሩ የማይሳናችሁ የለም" ብሎ ገልብጦ ዙሪያችንን በስህተት አማራጮች አጭቆ የምጣድ ብልጭልጭታ ያህል ጥፋት እንድንሠራ አድብቶና ጸንቶ ይጠብቀናል።

በጣም በእርግጠኝነት የምነግራችሁ፤ በዚህ የወሲብ ፊልም ጥገኝት እስራት ውስጥ ብትሆኑም፤ የሆነች ያህል ድርሻ ደግሞ እኛ በራሳችን ፍላጎት ወደን እንሳብበታለንም። ለዚህ እኮ ነው አስቀድሜ በ6 ክፍሎች ትምህርት በኩል የወሲብ ፊልምን እውነተኛ የመናፍስት ገጽታና ጠንቅ ላሳያችሁ የሞከርኩት። በሙሉ ሰብአዊ ልብ እንድትጸየፉት ነው መረጃው የተሰጣችሁ። በውስጥህ በሰናፍጭ ቅንጣትም ያህል ሳትጸየፈው ከተገኘህ፤ መንፈሱ የርሱን ፈቃድ የሚወክል ያንተን ፍቃድ አግኝቷልና ትንሿን ፍም ፍላጎት አረገብግቦ በወጥመድ እሳት መጣድ ቀላል ይሆንለታል። ከውስጥህ ግን ምንም መሻት ከሌለ፤ መንፈሱ አዚማዊ ጥያቄዎችን ገና ከውስጥህ ሲፈጥራቸው ትለየዋለህ። ምክንያት? ያንተ አይደለማ። ባንተ ውስጥ የሚመላሰውን ያንተ መሰል የመንፈስ አሳብን ሰንጥቆ ለመለየት፤ በፍጹም መሻት የዝሙት ሕይወቱን መጥላትህ አቅም ይሆንሃል። ትንሽም ብትሆን የራስህ ፍላጎት ከተገኘ፤ ይሄንን አውጥተህ እስከትጥል ድረስ እግዚአብሔርም ዝም ይላል። በፈቃድህ በኩል የሚያድን አባት ነውና። የመናፍስትን ውጊያ ለማስቆም የኛ የውስጥ ፍላጎትና የእምልኮት ልምምድ አንድ ቦታ ላይ መገናኘት አለባቸው። ብዙዎቻችን አንድ እግራችን ወደ እግዚአብሔር መመለስ ላይ፤ አንዱ ደሞ አለመመለስ ላይ ረግጦ ነው ወደፊትም ወደኋላም እየሄድን የምንቸገረው። ስለዚህ መጠየቅ አለባችሁ። ዘመናትን የበጠበጣችሁን ይሄ ጨካኝና ክፉ ጠላት ለማስቆሞ ምን ያህል ትፈልጋላችሁ? ይሄ የፍላጎታችሁ መጠን ልክ ከፍ ሲል የአምልኮት ልምምዱ በራሱ ይጣፍጣችኋል። የውስጥ ፍላጎቱ ነው በሥጋችን የውጪ ገጽታ በኩል አምልኮታችን ላይ የሚተረጎመው። ክፋትን የመሸሽ ፍላጎትህ ላይ ጥያቄ ኖርብህ ክፋትን ስትቀጠቅጠው ብትውል እርሱን የሚወክል ምሽግ አግኝቶብሃልና ተዳክሞም እንኳን ቢሆን ይፋለማል። ስለዚህ ውጊያው የኛን ባሕሪይ ጭምር ከማረም ጋር የተያያዘ ሂደት አለው።

## <u>❺· መቆጠብ</u>

ይሄኛው ደግሞ መንፈስ የሚመጣበትን መንገድ አስቀድሞ የመዝጊያ መፍትሔ ነው። አንድ ግልጽ አስተንትኖት የማይሻ ጉዳይ አለ። ርኩሰት የሚሰተናገድበት ቦታና ጊዜ ላይ ቆመህ ርኩሰት አይምጣብኝ አይሠራም። ክፉ የሚመላለስበት ሥፍራ ላይ ተገኝተህ ክፉ አይንካኝ አይሆንም። ስለዚህ የወሲብ ፊልሞች የሚመላለሱባቸው መንገዶች ላይ ቆማችሁ፤ መልሶ ደግሞ በእስራቱ ተቸገርኩኝ አይሠራም። ከምታየው ነገር የተነሣ ዕብድ ትሆናለህ" የሚለው ቃል ከተገኘ፤ ከውጪ ወደ ውስጥ የምታስገባቸውን ማንኛውንም አይነት መረጃዎችን መቆጠብ ግዴታ ይሆናል። ምን ማለት ነው ሲባል፥ እነዚህን የእርግማን ትዕይንቶች ወደ ሕይወታችን የመሳቢያ መንገዶች ማለትም ሙዚቃዎች፣ ፊልሞች፣ ጽሑፎችና ሌሎች መዝናኛዎችን እያተከታተሉ በዚህ ጋር ደግሞ ነጥሎ የዝሙት ፊልሞቹን ማስቆም አይቻልም። ለዚህ ነው በክፍል 3 እና 4 ትምህርታችን እነዚህን ለዝሙት ኢንዱስትሪዎች ማገዣ ድልድዮችን እንድታፈርሱ መረጃ የተሰጠው።

በቀላሉ የፍትወት ስሜቶችን የሚጠሩ መዝናኛዎችን፣ ቋንቋዎችንና ጸባል ሱሶችን ይዞ፤ ከመናፍስቱ አዚማዊ ፊልሞች መላቀቅ አይቻልም። አልሸሽም ዘወር አሉ መዝናኛዎችን እያስተናገዱ፤ በሌላ በኩል ችግሩ አልተወኝም አብሮ አይስማማም። ከላይ ለዚህ ነው ሙሉ ፍላጎት ሲኖረን ነው መናፍስቱን ማስቆሞ የሚቻለው የምለው። ከተያያዥ  መዝናኛዎችና ድርጊቶች ለመቆጠብ፤ ከእጅ ሥልካችንና ኮምፒውተራችን ላይ ጸምስሰን ስናጠፋቸው፤ መናፍስቱ እንደ ግብር ይጠይቁ ዘንድ ወደኛ የቅጽበትም ትሁን የሚያገኙት ምክንያት ስለሚዘጋባቸው የውስጥ ግፊቱን በቀላሉ ማሸሽ እንችላለን።

❻· ዙሪያውን በእግዚአብሔር ነገራት መሙላት

በመፍትሔ አምስት ላይ የተጠቀሰውን የመቆጠብ መንገድ ስንጓዝበት፤ ጎን ለጎን በተቆጠብንባቸው ቦታዎች ላይ ምትክ አድርገን የእግዚአብሔርን ነገራት መሙላት ነው። ሙዚቃውን ስትከለክል በምትኩ ዝማሬዎችን መፍቀድ ነው። አመፃ ፊልሞችንና መዝናኛዎችን ስትከለክል በምትኩ መንፈሳዊ ትምህርቶችን መፍቀድ ነው። አጠር ባለ ቋንቋ ጊዜያችን ሁሉ በሰማያዊ ገጽታዎች እየተወረሰ ሲመጣ፤ ምድራዊያኑ ማታለያዎች የኛን የሥጋ ፍቃድ የሚገዙበት መንገድ ያጣሉ። ስለዚህ መንፈሳዊነትን በዘርፈ ብዙ አቅጣጫዎች ማሳደግ አስፈላጊ ነው።

አስጀምሮ ያስፈጸመን ልዑል እግዚአብሔር ስሙ ለዘላለም የተመሰገነ ይሁን።

# በማለዳ ንቁ